

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ፍትሐ ነገሥትን የተማሩ ሊቃውንት ከሁሉ የከበሩ ተደርገው ይታዩ ነበር። ስያሜያቸውም "ሊቄ" ይባል ነበር። ነገሥታት በፍርድ እንዳያዳሉ አንቀጽ ጠቅሰው ከብሉይ ከሐዲስ አመሳክረው የሚፈርዱ ሊቃውንት ነበሩ። ሠለስቱ ምእት (ሦስት መቶ አስራ ስምንቱ ቅዱሳን ሊቃውንት) ለጊዜው ለንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ፍጻሜው ግን ሁሉም ነገሥታት ይመሩበት ዘንድ የሰሩልን የሕግ መጽሐፍ ነው። ከዚያም በኋላ በተለያዩ ጊዜያት የተነሱ ቅዱሳን አባቶች በአካባቢያዊ ሲኖዶስ የሰሯቸውን ቀኖናዎች አጠቃሎ የያዘ ነው። ሁለት ክፍል አለው። አንደኛው ክፍል ፍትሕ መንፈሳዊ ይባላል። ቤተክርስቲያን የምትመራበትን የጾም የጸሎት የምጽዋት የክህነት የጥምቀት የአስራት እና የመሳሰሉ ጉዳዮዎችን የያዘ ነው። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ነገሥታት ሕዝቡን እንዴት ማስተዳደር እንዳለባቸው የሚገልጽ ሲሆን በተጨማሪም ስለሚበሉ እና ስለማይበሉ ነገሮች ስለ ጋብቻ ስለ ነገሥታት ስለዳኞች ስለ ውርስ እና ስለመሳሰሉት የሚናገር ነው። ፍትሐ ነገሥት ስያሜውን በሁለተኛው ክፍል አግኝቶታል።

አንቀጽ ፩

ስለቤተክርስቲያን ይናገራል። በቤተክርስቲያን ውስጥ ዓለማዊ ነገር መነጋገር አይገባም። ዋዘ ፈዛዛ መናገር አይገባም። ዋዘ ፈዛዛ ነገርንስ በጸናው መናገሩ ነው እንጂ ከቤተክርስቲያን ውጭም አይገባም። እግዚአብሔር እድሜን የሰጠን መልካም ሥራ ሰርተንበት ለዘለዓለማዊው ሕይወት ስንቅ እንድንሰበስብበት እና ለዚያ የሚያበቃ መልካም ሥራ እንድንሰራበት ነው። ቤተክርስቲያን ውስጥ መሳቅ መጫወት አይገባም። ቤተክርስቲያን የጸሎት ቤት ናት። ጸሎትን እግዚአብሔር በማንኛውም ቦታ ይሰማል። ቤተክርስቲያን ደግሞ በተለየ ጸጋውን የሚያድልባት የጸጋው ግምጃ ቤት ናት። ቤተክርስቲያን ውስጥ ጸሎት ስናደርግ ሌላውን እንዳንረብሽ በቀስታ እንጸልይ። ኢትክላሕ በሕቁ አላ ዘምር በመጠን እንዲል።

በማንኛውንም ሕንጻ ቤተክርስቲያን የምእመናንን ጸሎት ለማሳረግ እግዚአብሔርን ለማመስገን በምልጃቸው በጥበቃቸው የሚረዱን ቀን 600 ቅዱሳን መላእክት ሌሊት 600 ቅዱሳን መላእክት አሉ። ቤተክርስቲያን ሊሰራ ሲታሰብ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ መፍቀድ አለበት። እርሱ ሳይፈቅድ አይሰራም። ታቦት ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚችል መሆን አለበት። በሐዲስ ኪዳን ታቦትን የምናከብርበት ምክንያት የክርስቶስ ሥጋና ደም ስለሚፈተትበት ነው። ለእግዚአብሔር ሥም ሁሉ ይገዛል ይሰግዳል እንዲል ደግሞ ታቦት ሥሙ የተጻፈበት ነውና ለታቦቱ የጸጋ ስግደት እንሰግዳለን። ቤተክርስቲያንም ታቦትም ለአገልግሎት ከመዋላቸው በፊት በሜሮን መክበር አለባቸው። የቤተክርስቲያንን ንዋያት ከቤት ወስዶ ለግል ዓላማ ማዋል ክልክል ነው። ብልጣሶር በጽዋው ቢጠጣበት ተቀስፏልና።

የሐዋርያት መልእክት የጳውሎስ መልእክት ሲነበብ ጧፍ ይበራል። እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ የሚለውን ለመግለጥ ነው። ወንጌል ሲነበብም የበለጠ ጧፍ ይበራል። ጌታን የዓለም ብርሃን ይለዋልና ነው። በችግር ጊዜ ምእመናን ዓላውያን ተነስተውባቸው ቤተክርስቲያን መሄድ ባይችሉ ከጳጳሱ ቤት ሄደው ቀድሶ ያቆርባቸዋል። ታቦት በሌለበት ቤተክርስቲያን አይቀደስም። ቤተክርስቲያን ውስጥ መሸጥ አይቻልም። ቤተክርስቲያን ቅጽር ውስጥ የሌላ እምነት ተከታዮች መግባት አይችሉም። ይህንን የሚጠብቅ ዘበኛ (አጻዌ ኆኅት) አለ።

ክፍል ፪ ይቀጥላል።

እስካሁን በአንድ ላይ አልታተመም። በተለምዶ 72ቱን ነው 81ዱ እየተባለ እየተሸጠ ያለው። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፪ እንዲህ ይዘረዝራቸዋል።

1) ዲድስቅልያ

2) መጽሐፈ ቀሌምንጦስ

3) አብጥሊስ

4) ሥርዐተ ጽዮን

5) ትእዛዝ

6) መጽሐፈ ኪዳን ፩

7) መጽሐፈ ኪዳን ፪

8) ግጽው

9) የማቴዎስ ወንጌል

10) የማርቆስ ወንጌል

11) የሉቃስ ወንጌል

12) የዮሐንስ ወንጌል

13) የሐዋርያት ሥራ

14) ራእየ ዮሐንስ

15) የጴጥሮስ መልእክት ፩

16) የጴጥሮስ መልእክት ፪

17) የዮሐንስ መልእክት ፩

18) የዮሐንስ መልእክት ፪

19) የዮሐንስ መልእክት ፫

20) የይሁዳ መልእክት

21) የያዕቆብ መልእክት

22) የጳውሎስ መልእክት ዕብራውያን

23) የጳውሎስ መልእክት ሮሜ

24) የጳውሎስ መልእክት ኤፌሶን

25) የጳውሎስ መልእክት ገላትያ

26) የጳውሎስ መልእክት ቲቶ

27) የጳውሎስ መልእክት ፊልሞና

28) የጳውሎስ መልእክት ጢሞቴዎስ ፩

29) የጳውሎስ መልእክት ጢሞቴዎስ ፪

30) የጳውሎስ መልእክት ቆሮንቶስ ፩

31) የጳውሎስ መልእክት ቆሮንቶስ ፪

32) የጳውሎስ መልእክት ፊልጵስዩስ

33) የጳውሎስ መልእክት ቆላስይስ

34) የጳውሎስ መልእክት ተሰሎንቄ ፩

35) የጳውሎስ መልእክት ተሰሎንቄ ፪

1) ኦሪት ዘፍጥረት (ዘልደት)

2) ኦሪት ዘጸአት

3) ኦሪት ዘሌዋውያን

4) ኦሪት ዘኍልቁ

5) ኦሪት ዘዳግም

6) መጽሐፈ ኢያሱ

7) መጽሐፈ ሩት

8) መጽሐፈ መሳፍንት

9) መጽሐፈ ኢዮብ

10) መጽሐፈ እስቴር

11) መጽሐፈ ጦቢት

12) መጽሐፈ ዮዲት

13) አንደኛ ሳሙኤል

14) ሁለተኛ ሳሙኤል

15) አንደኛ ነገሥት

16) ሁለተኛ ነገሥት

17) አንደኛ ዜና መዋእል

18) ሁለተኛ ዜና መዋእል

19) መዝሙረ ዳዊት

20) መጽሐፈ ሲራክ

21) መጽሐፈ ምሳሌ

22) መጽሐፈ ተግሣጽ

23) መጽሐፈ ጥበብ

24) መጽሐፈ መክብብ

25) መኃልየ መኃልይ

26) ትንቢተ ኢሳይያስ

27) ትንቢተ ኤርምያስ

28) ትንቢተ ሕዝቅኤል

29) ትንቢተ ዳንኤል

30) ትንቢተ ሆሴዕ

31) ትንቢተ አሞጽ

32) ትንቢተ ሚክያስ

33) ትንቢተ ኢዩኤል

34) ትንቢተ አብድዩ

35) ትንቢተ ዮናስ

36) ትንቢተ ናሆም

37) ትንቢተ ዕንባቆም

38) ትንቢተ ሶፎንያስ

39) ትንቢተ ሐጌ

40) ትንቢተ ዘካርያስ

41) ትንቢተ ሚልክያስ

42) አንደኛ መቃብያን

43) ሁለተኛ መቃብያን

44) መጽሐፈ ዕዝራ

45) መጽሐፈ ዕዝራ ካልእ

46) ዜና አይሁድ

ሦስተኛ መቃብያን ከሁለተኛ መቃብያን ጋር አንድ ተብሎ ይቆጠራል። መጽሐፈ ነህምያ እና መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል በመጽሐፈ ዕዝራ ተካቶ ይቆጠራል።መጽሐፈ ኩፋሌ ከኦሪት ዘፍጥረት ጋር አንድ ተብሎ ይቆጠራል። መጽሐፈ ሄኖክን ሐዋርያት የመጽሐፉን ደግነት አይተው በከመ ይቤ ሄኖክ እያሉ ጽፈዋል። ከአስራው ግን አላስገቡትም። ሄኖክ እና ኩፋሌን ለየብቻ ከቆጠርን ግን መጽሐፈ ሳሙኤል ሁለቱ በአንድ መጽሐፈ ነገሥት ሁለቱ በአንድ ይቆጠራሉ። መጽሐፈ ባሮክ፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ፣ ተረፈ ኤርምያስ እና ተረፈ ባሮክ ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር አንድ ተብለው ይቆጠራሉ። መጽሐፈ ሶስና ከትንቢተ ዳንኤል ጋር አንድ ተብሎ ይቆጠራል።

ዘእዙዝ ተወክፎቶን የተባሉ መጻሕፍት አምላካውያት የተባሉ እኒህ ናቸው። ሌላ አዋልድ መጽሐፍ ቢጻፍ ተቀባይነት የሚኖረው በእነዚህ ተገምግሞ ነው። 81ዱን የማይቃወም ሆኖ ሲገኝ በምሥጢር ከ81ዱ ጋር ሲገናኝ አዋልድ ይባላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ማለት ነውና ልጅ አባቱን እንዲመስል አዋልድ መጻሕፍትም 81ዱን መምሰል አለባቸው።መጻሕፍትን ማንበብ ወደ ሕይወት መንገድ ይመራሉ። ብዙ ቅዱሳን አንባቢዎች ነበሩ። ማንበባቸው ወደ መልካም ነገር መርቷቸዋል። ቅድስት ድንግል ማርያም አንባቢ ነበረች። መዝ-86 "እግዚአብሔር ለሕዝቡ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል" እንደተባለ ማስታዎስ ይገባል።

መጻሕፍተ መነኮሳት የሚባሉት:-

1) ማር ይሥሐቅ

2) ፊልክስዩስ

3) አረጋዊ መንፈሳዊ

መጻሕፍተ ሊቃውንት የሚባሉት ደግሞ:-

1) ሃይማኖተ አበው

2) ፍትሐ ነገሥት

3) ድርሳነ ቄርሎስ

4) ውዳሴ ማርያም

5) 13ቱ ቅዳሴ

6) ተግሣፀ ዮሐንስ አፈወርቅ

7) ድርሳነ ዮሐንስ አፈወርቅ

8) መቅድመ ወንጌል

9) አቡሻህር

ናቸው። አራቱ ጉባኤያት የሚባሉ እኒህ ናቸው።

ፍትሐ ነገሥት ክፍል 3

ሴት ወንድን ልጅ ክርስትና ማንሳት አትችልም። ወንድ ልጅም ሴት ልጅን ክርስትና ማንሳት አይቻልም። ሴት ሴት ልጅን ወንድ ወንድ ልጅን ያነሳል እንጂ። ባለማወቅ ይህንን እስካሁን አድርገን ይሆናል። ለወደፊት ይህንን እናሳውቅ። ዲድስቅልያ ፴፬ ኢይትወከፉ እደው አንስተ ወኢአንስት እደወ አላ ይትወከፉ ተባዕት ተባዕተ ወአንስት ይትወከፉ አንስተ እንዲል። ክርስትና እናት ወይም ክርስትና አባት ያስፈለገው ሕጻኑን የሃይማኖት ትምህርት ከልጅነቱ ጀምሮ እንዲያስተምረው ነው። ለሌላ አይደለም።

ማጥመቅ የሚችሉ ጳጳሳትና ቀሳውስት ብቻ ናቸው። ዲያቆን ማጥመቅ አይችልም። ከዓላውያን (ትክክለኛ ሃይማኖት ከሌላቸው ሰዎች) የተጠመቀ ሰው ቢኖር ተጠመቀ አይባልም። ልጅነት አገኘ አይባልም።ረስጣ ፵፬ ወለእመቦ ብእሲ ዘተወክፈ ጥምቀተ እምዓላውያን ኢኮነ ውእቱ ምእመነ እንዲል ልጅነት የሚገኘው በትክክለኛዋ ሃይማኖት አምነው ሲጠመቁ ነው። ማር:16;16 ያመነ የተጠመቀ ይድናል እንዲል።

የልጅነት ጥምቀትን ያልተጠመቀ ሰው መንግሥተ ሰማያት አይገባም። ሕጻኑ ለመጠመቅ ጊዜው ከደረሰ በኋላ ዕለቱን ማሳለፍ አይገባም። ጥምቀት በቄስም በጳጳስም ብንጠመቅ ያው አንዲት ናት። በሁለቱም አድሮ ልጅነትን የሚያድል አንዱ እግዚአብሔር ነውና። ትልቅ ከሆኑ በኋላ የሚጠመቁ ሰዎች ከመጠመቃቸው በፊት እምነታቸውን በቄሱ ፊት ራሳቸው ይመስክሩ። ሕጻናት ከሆኑ ግን ሕጻኑን የሃይማኖት ትምህርት ለማስተማር ክርስትና የሚያነሳው ሰው ይመስክርለት።

መጀመሪያ ሕጻናትን ማጥመቅ ይገባል። ከዚያ ንዑሰ ክርስቲያን ይጠመቃል። ንዑሰ ክርስቲያን የሚባለው ከአደገ በኋላ በሌላ ሃይማኖት ቆይቶ የሚጠመቅ ነው። የጸነሱ ሴቶችም ሲጠመቁ ጥምቀቱ ለራሳቸው ብቻ እንጂ በማኅፀናቸው ላለው ልጅ አይተርፍም። ንዑሰ ክርስቲያን ሲጠመቅ የአንገት የእጅ የጆሮ አጠቃላይ ጌጣጌጡን ሁሉ ያወልቃል። ወንድ ልጅ 40 ቀን ሲሞላው ይጠመቃል። ሴት ልጅ 80 ቀን ሲሞላት ትጠመቃለች። ነገር ግን ሕጻኑ 40/80 ቀን ሳይሞላቸው ለሞት የሚያደርስ ጽኑ ሕመም ካመማቸው ቀኑ ሳይሞላ በሞግዚት ወደ ቤተክርስቲያን ወስደው ያስጠምቋቸው።

ሴት እና ወንድ ልጅ መንታ ቢወለዱ ወንዱን 40 ቀን ሲሞላው በሞግዚት ወስደው ያጠምቁታል። ሴቷ ደግሞ ቀኗ ሲሞላ እናቷ ወስዳ ታስጠምቃታለች። የሴትም የወንድም ጾታ ያለው ፍናፍንት ቢወለድ በሚሸናበት ጾታ ማለትም በወንድ አባል የሚሸና ከሆነ በ40 ቀን በሴት ከሆነ በ80 ቀን ያጥምቁት። ሕጻናት የሚጠመቁበት ማይ ካህኑ በጸለየበት ጊዜ ከጌታ ጎን የፈሰሰውን ማየ ገቦ ይሆናል። ስለዚህ ከዚያ የተረፈውን ለምእመናን መርጨት አይገባም።

ሴት ልጅ ከወለደች በኋላ ጸበል እስክትረጭ እስላም ናት የሚሉ ሰዎች አሉ። ትልቅ ስህተት ነው። ልጅ መውለድ እስላም አያደርግም። በአስረኛው ቀን በሰባተኛው ቀን ወዘተ ካህን መጥቶ ጸበል ይረጫል። የሚረጨው ግን የተጸለየበት ጸበል መልካም ስለሆነ እንጂ በአስረኛው ቀን ተረጩ አልተረጩ ነውር ሆኖ አይደለም። ሕጻኑ ከተጠመቀ በኋላ ሜሮን ይቀባል። ጌታ ወደ ግብጽ በተሰደደ ጊዜ ወዙ ከነጠበበት በለሳን የሚባል ተክል በቀለበት። ሐዋርያት የዚህን ቅርፍት ቀርፍተው የመስቀሉን እጣቢ በአዲስ ሸክላ አድርገው ይጸልዩበታል። በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ይፈላል።

ጥያቄ ካለ አምጡት

ፓትርያርክ/ሊቀ ጳጳሳት ያለ ኤጲስ ቆጶሳት እና ጳጳሳት ጉባኤ አይሾምም። እገሌ ይሾም እገሌ ይሾም የሚል ክርክር ቢነሳ ውሳኔው ብዙዎች ባሉት ይጸድቃል። በሊቀ ጳጳሳት ላይ በደል ቢገኝበት የአንድን ጳጳስ ምስክርነት ብቻ አይተው ዳኝነት አይሰጡበት። ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ጳጳስ በሕይወት እያለም ከሞተ በኋላም ውግዘቱን አይፈታውም። ጳጳስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ በሕይወት እያለም ከሞተ በኋላም ውግዘቱን አይፈታውም። ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ቄስ ሳለም ከሞተም በኋላ አይፈታውም። ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ሊቀ ጳጳሳት ከሞተ በኋላ ይፈታዋል። ጳጳስ ያወገዘውን ጳጳስ ቄስ ያወገዘውን ቄስ ከሞተ በኋላ ይፈታዋል። ቄስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ጳጳስ ጳጳስ ያወገዘውን ሊቀ ጳጳሳት ሳለም ከሞተም በኋላም መፍታት ይችላል። ለመለየት ያህል እንዲረዳን ሊቀ ጳጳሳት የሚባለው ፓትርያርኩ ነው። ጳጳስ የሚባሉት ደግሞ በኤጲስ ቆጶሳት ላይ የተሾሙ ናቸው። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በሀገራችን ኢትዮጵያ ጳጳስ የሚባሉት በየሀገረ ስብከቱ ያሉት ናቸው። እነርሱ የሚመሯቸው ኤጲስ ቆጶሳት ግን የሉም። ይህ ጳጳስ በሌላ አገላለጽ መጥሮጶሊስ ይባላል። በምሳሌ ብናየው በየአውራጃው ላለው ኤጲስ ቆጶሳት ይሾማሉ። እንዲህ ከሆነ አውራጃዎች ከፍ ብለው ክፍለ ሀገር ይሆናል። የየአውራጃዎቹ ኤጲስ ቆጶሳት ኃላፊ የክፍለ ሀገሩ ይሆናል። ስሙንም መጥሮጶሊስ ዘውእቱ ጳጳስ ይለዋል። ከዚያ ለየክፍለ ሀገሮች ጳጳሳት በሹመት የበላያቸው የሀገሪቱ ሊቀጳጳሳት ወይም ፓትርያርክ ይሆናል ማለት ነው።

ሊቀ ጳጳሳትን የሚመርጡ ሰዎች ምግባራቸው የተመሰከረላቸው እውነተኞች ሊሆኑ ይገባል። ዘመኑ ከኃድያን የበዙበት ከሆነ መጽሐፍ አዋቂውን ሊሾሙት ይገባል። ዘመኑ የረኀብ የመከራ ዘመን ከሆነ አስተዳደር አዋቂውን ሊሾሙት ይገባል። የማይገባውን ቢሾሙ በደሉ በሿሚዎች ይሆናል። ተሿሚው ጳጳስ ሰላምን የሚያስጠብቅ ደዌ የሌለበት ማየት መስማት መናገር መሄድ የሚችል የተማረ መሆን አለበት። ሁለት ጳጳሳት ለሊቀ ጵጵስና እኩል የተገቡ ሆነው ቢገኙ በእጣ ይለዩዋቸው። በአንድ ጊዜ ሁለት ፓትርያርክ መሾም አይገባም። በተለያየ ምክንያት ተሹመው ቢገኙ መጀመርያ ለተሾመው ትጸናለች።

ምእመናን የፓትርያርካቸውን ስሙን ግብሩን ጠባዩን ማወቅ አለባቸው። ፓትርያርክም አምስት ነገሮች ሊኖሩት ይገባል። እነዚህም ሃይማኖትን መጠበቅ፣ በእውነት መፍረድ፣ ለሚገባቸው መመጽወት፣ ሹመት የሚገባውን መሾም፣ ምእመናን የሚሠሩትን ሥራ መመርመር ናቸው። ፓትርያርክ ቢታመም እስኪሻለው ይጠብቁት፣ ደዌው ለብዙ ዘመን ከጸናበት ሌላ ይሾማል። ቆይቶ ቢሻለው ግን በእርሱ ቦታ የተሾመው በፈቃዱ ሹመቱን ሊለቅለት ይገባል። የአእምሮ በሽተኛም ከሆነ እና ሃይማኖቱን ከካደ ይሻራል። ጳጳሳትን ልናከብራቸው ይገባል። በዘመናችን ጳጳሳትን መምህራንን መሳደብ እንደ ጀብድ እየተቆጠረ ነው። ከላይ እንዳየነው እንኳን ምእመን አንድ ጳጳስ እንኳ በፓትርያርክ ላይ ነውር አየሁ ቢል የአንድን ጳጳስ ምስክርነት አይስሙ ተብሏል። ስለዚህ ጥፋት ያየን ቢመስለን እንኳ በየማህበራዊ ሚድያው ስማቸውን ማጥላላት አይገባም። ችግር ካየን ለሲኖዶስ ሙሉ ማስረጃ ይዘን መቅረብ ነው ያለብን። አባትን መሳደብ ውርደት ነውና።

ክፍል ፰ ይቀጥላል።

ስለ ኤጲስ ቆጶሳት ይናገራል። ኤጲስ ቆጶስ:-

@ ጉቦ ከፍሎ የተሾመ ኤጲስ ቆጶስ ካለ ከሹመቱ ይሻር። የሾሙት ኤጲስ ቆጶሳትም ይሻሩ።

@ ከሀገረ ስብከቱ ውጪ ክህነት የሰጠ ይሻር። ከሀገረ ስብከታቸው ውጭ የሚሾሙ ካህናትም ይሻሩ።

@ በዚህ ዓለም መኳንንት እንዲሁም ነገስታት ኃይልና እርዳታ የተሾመ ይሻር።በመንግስት ትእዛዝ የተሾመ ይሻር።

@ የኃጢኣተኛን ንሥሓ አልቀበልም የሚል ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር ይሻር።

@ አራጣ የሚቀበልና ነገር ሰርቶ ሰውን ከሰው የሚያጣላ ይሻር።

@ ዝሙት የሰራ ኤጲስ ቆጶስ ካለ ይሻር።

@ ዓለማዊ ሥራን የሚሰራ ጳጳስ ከሹመቱ ይሻር።

@ 50 ዓመት የሆነው ሰው ይሾም። 50 ዓመት የሆነው ባይገኝ ለሹመት የበቃ ሆኖ ከተገኝ ከ50 ዓመት በታች ያለውንም ይሹሙት

@ ፓትርያርኩ ሳይጽፉለት ወይም ሳይፈቅዱለት ወደ ንጉሡ የሄደ ጳጳስ ይሻር።

@ ለመፈራት ብለው ሰውን የሚደበድቡ ወይም የሚማቱ ቀሳውስት ዲያቆናት እና ጳጳሳት ይሻሩ።

@ የጠንቋዮችን ነገር አምኖ የሚቀበል እንዲሁም ኮከብ ቆጣሪ እና ለጥንቆላ ቅጠል የሚበጥስ ይሻር።

@ ከሐራጥቃ ጥምቀትን የተቀብለ ወይም የቆረበ እንዲሁም በቦታ ከእነርሱ ጋር የጸለየ ይሻር።

@ ኤጲስ ቆጶሳት የተሾሙበትን ሀገረ ስብከት ትተው በሌላ ቦታ የትንሣኤን በዓል ካከበሩ ይሻሩ።

@ ሁለት ጊዜ የተሾመ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ይሻር።

@ ቆሞስ የኤጲስ ቆጶስ ተወራጅ ነው። በኤጲስ ቆጶስ ትእዛዝ መሰረት ይሰራል።

@ ኤጲስ ቆጶስ ቀሳውስትን ይባርክ እንጂ እርሱ በቀሳውስት አይባረክ። የክርስቶስን ሥጋውን ደሙንም ከኤጲስ ቆጶሳት ይቀበል እንጂ ከቀሳውስት አይቀበል።

@ የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሁን። ይኸውም ጥቅምት 12 እና ከትንሳኤ በኋላ በ28ኛው ቀን ነው። በጉባኤውም አንድ መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ወንበር ይቀመጥ

@ ኤጲስ ቆጶስ የተቸገሩትን ይርዳ። ሕዝቡ እየተራበ እየተቸገረ እርሱ ማእደ ሥጋውን የሚያሳምር አለባበሱን የሚያስጌጥ ጳጳስ አይባልም።

@ መሥዋእት ሠው ተው ጸሎት ጸልየው ወደ እግዚአብሔር የሚያማልዷችሁ ናቸውና ኤጲስ ቆጶሳትን አክብሩ።

@ በቀለኛ ጳጳስ ጳጳስ አይባልም።

@ በቅዳሴ ጊዜ የኤጲስ ቆጶሱን ሥም ይጥሩ።

@ ኤጲስ ቆጶሳት የበደለውን ይገሥጹ

@ ኤጲስ ቆጶሳት ያልተማሩትን ያስተምሩ ያመኑትን ያጽኑ።

@ ኤጲስ ቆጶስ ሆይ ሽማግሌዎችን አረጋጋቸው እንጂ አታሳዝን።

@ ኤጲስ ቆጶስ ሆይ ሽማግሌዎችን እንደ አባትህ ደስ አሰኛቸው። ወጣቶችን እንደ ወንድሞችህ እያቸው። ቆነጃጅትን እንደ እህቶችህ እያቸው። ባልቴቶችን እንደ እናትህ እያቸው። እናት አባት የሌላቸውንም እንደ እናት እንደ አባት ሆነህ ደስ አሰኛቸው።

@ ኤጲስ ቆጶስ አንዱንስ እንኳ ሳይመረምር መሾም የለበትም።

@ ኤጲስ ቆጶስ ከንቱ የሆነ የዚህን ዓለም ነገር አይስማ።

@ ኤጲስ ቆጶስ የላመ የጣመ አይቅመስ። የሞቀ የደመቀ አይልበስ።

@ ኤጲስ ቆጶስ ነዳያንን እየጠላ ባለጸጎችን አይውደድ።

@ ኤጲስ ቆጶስ ወደ አሕዛብ በዓል አይሂድ። በአነጋገር በሥራ ለምእመናን አርዓያ ይሁን።

@ ኤጲስ ቆጶስ ልቡ እንዳይገዝፍ ሥጋ አይብላ። ጽኑ ደዌ ከታመመ ግን ዓሣ ይብላ። ወይንም ጥቂት ይጠጣ።

@ ራሱን የሰለበ ሰው ኤጲስ ቆጶስና አይሾም። በግድ ሌሎች ሰልበውት ከሆነ ግን ከሹመት አይከልከል።

@ ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ ሶስት ሱባኤ ይጹም።

@ ዕውር፣ መናገር የማይችል፣ መስማት የማይችል፣ ኤጲስ ቆጶስነት አይሾም።

@ ኤጲስ ቆጶስን ቢገኙ ሦስት ባይገኙ ሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ይሹሙት።

@ ኤጲስ ቆጶስናን ድንግልና ከምንኩስና ያለው ሰው ይሾም። ቢታጣ ግን ሕዝባዊ ይሁን

@ ኤጲስ ቆጶስ ለሰው የሚያዝን የሚራራ፣ ልቡናው ከቂም ከበቀል ከክሕደት የተለየ፣ በበጎ ሥርዓት ሁሉ የጸና ይሁን።

ክፍል ፮ ይቀጥላል።

ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 6

ስለ ቀሳውስት ይናገራል።

© ቄስ ሚስቱ ብትወልድ ከአገልግሎት አይከልከል። ደም ካልነካው መቀደስ ይችላል።

© ቄስ ወይም ዲያቆን እግዚአብሔርን አገለግላለሁ በማለት ከሚስቱ መለየት አይገባውም። ተባሕትዎ እይዛለሁ ወይም እመነኩሳለሁ ብሎ ሚስቱን ቢተዋት ከክህነቱ ይሻር።

© በገበያ መካከል የሚበላ ቄስ፣ ከመሸታ ቤት ገብቶ የሚጠጣ ቄስ፣ ሞቶ የተገኘውን እና የአውሬ ትራፊን የሚበላ ቄስ ይሻር።

© ከሌላ ቤተእምነቶች የሚገባ፣ ለሥጋዊ ፈውስ ለመፈወስ ብሎ ወደ ዓላውያን ወደ ከኃድያን የሄደ፣ ከሌላ ቤተ እምነቶች በዓል ተገኝቶ ያከበረ፣ ለቤተ እምነታቸውም እጅ መንሻ ያገባ ቄስ ይሻር።

© ቄስ አንዲትን ሴት ያገባ ይሁን።

© ቄስ ቂመኛ፣ ሰካራም አይሁን

© ሠላሳ ዓመት ሳይሞላው ቄስ አይሾምም።

© መጻሕፍትን ያልተማረ ይልቁንም አራቱን ወንጌል ያልተማረ ቅስና አይሾም።

© የቄስ ሥልጣን ማስተማር፣ ማጥመቅ፣ መቀደስ እና መባረክ ነው።

© ቄስ ምእመናንን አውግዞ መለየት አይችልም። ነገር ግን ችግር ያለበትን ሰው ወደቤተክርስቲያን እንዳይገባ መከልከል ይችላል። አውግዞ መለየት የጳጳሳት ድርሻ ነው። ቄስ ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይገባ፣ በምእመናን መካከል እንዳይገኝ መገዘት ነው የሚችል።

© ቄስ ሐዋርያት ካስቀመጡት ቀኖና የወጣ በምእመናን ላይ አይጨምር።

© አንድ ቄስ ከነበረባት ቤተክርስቲያን ወደ ሌላ ቤተክርስቲያን ሲሄድ አይቀበሉት። ኤጲስ ቆጶሱ ከፈቀደለት ብቻ ይቀበሉት።

© ቀሳውስት ምእመናንን እንዳይቆርቡ መቆጣት አይገባቸውም። አንተ ገና ወጣት ነህ ወዘተ እያሉ መከልከል አይገባም። የሚከለክሉ ቢኖሩ ከሹመታቸው ይሻሩ።

© ቀሳውስት ምእመናንን ይጠብቁ፣ አምስቱን አእማደ ምሥጢርም ጠንቅቀው ያስተምሩ።

© ቄስ ወይም ዲያቆን ነውር ተገኝቶበት ከተሻረ በኋላ የክህነት ሥራ ደፍሮ ቢሰራ ከምእመናን ይለይ። ይህንን እያወቁ አብረውት ያገለገሉ ካህናትም ይሻሩ።

© ቀሳውስት በአንቀጸ ኤጲስ ቆጶሳት የተናገርናቸውን መልካም ሥራዎች የሚሰራ ከዚያ የተከለከሉትንም የማይሰራ መሆን አለበት።ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 7

ይህ አንቀጽ ስለዲያቆናት ይናገራል።

√ ዲያቆናት ህዱኣን ጸጥ ያሉና የሚታዘዙ ይሁኑ።

√ በፍጹም ደስታ ያገልግሉ።

√ ቁጡ ብስጩ አይሁኑ። ቁጣ አዋቂውን አላዋቂ ያደርጋልና።

√ ሀብታም ድሃ ብለው የማያዳሉ ይሁኑ።

√ ዲያቆናት ምእመናንን በፍጹም ክብር ያክብሩ።

√ በሮማውያን ሥርዓት ዲያቆን 25 ዓመት ሳይሞላው አይሾምም። በእኛ ሥርዓት ግን በቅቶ ከተገኘ ከ7 ዓመት ጀምሮ መሾም ይችላል።

√ በአንድ ቤተክርስቲያን ቢያንስ 7 ዲያቆናት ሊኖሩ ይገባል። ደብሩ ትልቅ ከሆነ ግን ከዚያም በላይ ይሆናል።

√ ከዲያቆናት ጀምረው ያሉ አገልጋዮች ከቤተክርስቲያን ገንዘብ ይመገቡ።

√ ዲያቆን የተቸገሩትን፣ የታመሙትን እየጎበኘ መረዳት ያለባቸውን ለኤጲስ ቆጶሱ ይንገረው።

√ በቤተክርስቲያን ውስጥ ምእመናን እንዳይስቁ፣ እንዳይተኙ፣ እንዳይሳለቁ ይቆጣጠራቸው።

√ ዲያቆን በምሳ ጊዜ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ከሌለ አቡነ ዘበሰማያትን ደግሞ ባርኮ ይስጥ።

√ ዲያቆን ሕዝቡን በአንብሮተ እድ አይባርክ።

√ ሁለት ሴት ያገባ ዲያቆን ይሻር።

√ ዲያቆናት ሲሾሙ እንመነኩሳለን ብለው ቢሳሉና ስለታቸውን ቢያፈርሱ ይሻሩ።

√ ሊቀዲያቆን ከሥልጣኑ በታች ላሉት አለቃ ነው። የኤጲስ ቆጶሱ ዋና ረዳት ነው።

::::::::::::::

ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8

ስለ ንፍቀ ዲያቆናት፣ አናጕንስጢስ፣ ዐጻዌ ኆኅት፣ መዘምር እና ዲያቆናዊት ይናገራል። እኒህ ሁሉም ንዋየ ቅድሳትን መንካት አልተፈቀደላቸውም።

¶ አናጕንስጢስ ማለት አንባቢ ማለት ነው። ንባብ ይፈተንና ኤጲስ ቆጶሱ እንዲሁ በቃል ይሾመዋል። አከናውኖ የሚያነብ፣ ታዛዥ፣ ነገር የማያበዛ፣ የንባብን ስልት ስልቱን ለይቶ የሚያውቀው ይሁን። የሚያነበውን በተግባር ለማዋል የሚተጋ ይሁን። አናጕንስጢስ ቢሰርቅ ዓመት ቆይቶ ቀኖናውን ጨርሶ ያንብብ። ከዚህ በኋላ ግን እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በዚሁ መዓርግ ይኑር። ሚስቱ ብትሞትበት ሁለተኛ ማግባት ይችላል።

¶ መዘምራን የሚባሉት ዳዊት ደጋሚዎች ናቸው። የመዘምራንም ሚስታቸው ብትሞት ሁለተኛ ማግባት ይችላሉ። በአንብሮተ እድ አይሾሙም።

¶ ንፍቀ ዲያቆንም በአንብሮተ እድ አይሾምም። እንዲሁ በቃል ጳጳሱ ይሾመዋል። ንፍቀ ዲያቆናት ረዳቶች እንደመሆናቸው ዲያቆናትን ይርዱ። ንፍቀ ዲያቆን ልብሰ ተክህኖ መልበስ አይገባውም።

¶ ዐጻውተ ኆዋኅው (በር ዘጊዎች) ወንዶች በሚገቡበት በር ቁመው ይጠብቁ። እኒህም ለአንዲት ሰዓት እንኳ ከበር መለየት አይገባቸውም።

¶ ዲያቆናዊት ሴት;- ከሴቶች ወገን ቅስና ዲቁና መሾም አይገባቸውም። ሴቶች ነገር አመላላሾች አይሁኑ። ዲያቆናዊትነት የምትሾም ሴት 60 ዓመት የሆናት ትሁን። በአንድ ወንድ ጸንታ የኖረች፣ ልጆቿን በሥርዓት ያሳደገች፣ በበጎ ሥራ ጸንታ የኖረች ትሁን። ወንድ የሴትን ዕርቃን ማየት አይገባውምና ትልቅ ሴት ስትጠመቅ ካህኑ ሜሮን ሲቀባ ከተጠማቂዋ ከአንገቷ በታች ያለውን አካላቷን የቄሱን እጅ ይዛ ሜሮን የምትቀባ ዲያቆናዊት ሴት ናት።ዲያቆናውያት ሴቶች ሴቶች የሚገቡበትን በር ይጠብቁ። ዲያቆናዊት ዲያቆን ሳያዛት ምንም ምን አትስራ። ዲያቆናዊት ሴት ሴቶችን ትገሥጽ ትምከር። ሴቶች ቃላቸውን ከፍ አድርገው አይጸልዩ።

¶ አሁን ላይ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከዲያቆን በታች ያሉት መዓርጎች ተግባር ላይ ሲውሉ አናይም። በቅዳሴ ጊዜም ንፍቅ ዲያቆን ተብሎ የሚገባው ያው ዲያቆኑ ነው። ከዲያቆን በታች ያሉት ንፍቀ ዲያቆንን ጨምሮ ወደ መቅደስ መግባት አይችሉም።

ረድኤት እግዚአብሔር አይለየን።

በእንተ ኩሎሙ ካህናት።ሀብተ ክህነት አስር ደረጃዎች አሉት።እነዚህም:-

√ ሊቀ ጳጳሳት (ፓትርያርክ)

√ ጳጳሳት

√ ኤጲስ ቆጶሳት

√ ቆሞሳት

√ ቀሳውስት

√ ዲያቆናት

√ ንፍቀ ዲያቆናት

√ አናጉንስጢስ

√ መዘምር

√ ዐጻውተ ኆኅት

በቅደም ተከተል እኒህ ናቸው።

√ዓይነ ስውር ክህነት መቀበል አይችልም። የማይችለው ነውር ሆኖ ሳይሆን ቀድሶ ማቅረብና የካህንን ሥራ መሥራት ስለማይችል ነው። አንድ ዓይና ወይም አንካሳ ግን ዞሮ ማጠን ከቻለ ማንበብ ከቻለ ካህን መሆን ይችላል።

√ ካህናትን ምእመናን መመገብ  እንዲችሉ አይብዙ። መጠነኛ ይሁኑ።

√ ሀብተ ክህነት ከሀብተ መንግሥት ትበልጣለች።

√ በከንቱ የሚራገም ሰው ቢኖር እርግማኑ በራሱ ይደርሳል። በከንቱ በተረገመው ሰው እርግማን አይደርስም።

√ እየጸለይን እያለ ሰው መጥቶ ቢያነጋግረን ክርስቲያን ቢሆን የያዝነው የጸሎት አንቀጽ ጨርሰን በአቡነ ዘበሰማያት አስረን እናናግረዋለን። ሌላ እምነት ያለው ከሆነ ግን ጸሎታችንን ጨርሰን በአቡነ ዘበሰማያት አስረን እናናግረዋለን።

√ ካህን ከተሾመ በኋላ ባለመድኃኒትም ቢሆን አንጥረኛም ቢሆን ወደ ዓለማዊ ሥራ አይመለስ።

√ ካህን ሥጋዊ ሹመት አይሾም።

√ በኤጲስ ቆጶስ ላይ ክፉ ቃል የተናገረ እነሆ እግዚአብሔርን በደለ።

√ ልጄ ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተማረህን ሰው አክብረው።

√ ራሱን የሰለበ ካህን ከመዓርጉ ይሻር።

√ በዝሙት፣ በስርቆት፣ በውሸት ሲምል የተገኘ ካህን ይሻር።

√ የቅስና መዓርግ ከተቀበለ በኋላ ሚስት ያገባ ይሻር።

√ ቄስ ቢሰክር ቢራቆት ሰባት ሱባኤ ከቤተክርስቲያን ወጥቶ ይቆይ። ከዚያ በኋላም ከእርሱ መዓርግ ባነሰ መዓርግ እያገለገለ አንድ ዓመት ይቆይ። ዲያቆን ቢሆን አምስት ሱባኤ ይውጣ። በንፍቀ ዲቁና እያገለገለ አራት ወር ይኑር።

√ ካህን እና ካህን ቢጣሉ እስኪታረቁ ቤተክርስቲያን አይግቡ።

√አንድ ካህን ወደሌላ ሀገር ሲሄድ የክህነት ደብዳቤውን ካላሳየ ካህን ብለው አይቀበሉት።

√ ካህን ሕጹጸ ምግባር ቢሆን እንኳ እግዚአብሔር በእርሱ አድሮ ጸጋውን ይሰጣል።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ስለ ሕዝባውያን ይናገራል።

√ ጥቋራት መጠቆር መከተብ አይገባም።

√ ወንድ ልጅ ጸጉሩን አያሳድግ።

√ ሰውነትን ጥብቅ አድርጎ የሚያሳይ ልብስ አትልበስ ትእምርተ ዝሙት ነውና።

√ ወንድ ልጅ ጺሙን አይላጭ

√ ሥራ ፈት ሆኖ መኖር አይገባም

√ ክፉ ምክር አትምከር።

√ ሕዝባዊ ለበረከት የመጣውን ኅብስት ቆርሶ መስጠት አይገባውም።

√ ክርስቲያን ሰርግ ቤት ሄዶ ለዘፈን ማጨብጨብ፣ መዝፈን አይገባውም።

√ ሁሉንም ሰው ከአንተ የከበረ እንደሆነ አስበህ ኑር።

√ ሁልጊዜም ንቁ መሆን አለብን።

√ ማንም ሰው በጎ ሥራ ሳይሠራ ክርስቲያን ነኝ አይባል።

√ የክርስቲያን አካሄዱ በክርስቶስ ትእዛዝ መሰረት ይሁን።

√ አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን ቃለ እግዚአብሔር አስተምሩ። ሥጋዊ ጥበብንም አስተምሯቸው።

√ ሴት ባሏን ትውደደው፣ ትፍራው፣ ታክብረው፣ ትታዘዘው። ወንዶችም ሚስቶቻችሁን አክብሯቸው። ባል ለሚስቱ ይራራላት እንጂ አይታበይባት።

√ ባል ሚስቱን ደስ ለማሰኘት የሚፋጠን ይሁን። ሴት ልጅ ትሑት ልትሆን ይገባል። ልጆቿን ለሞግዚት አትስጥ።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አስር

ስለ መነኮሳት የሚናገር አንቀጽ ነው

√ እውነተኛ ምንኩስና አስቀድመህ ዓይንህን ክፉ ከማየት ጆሮህን ክፉ ከመስማት ወስነህ ገትተህ ትይዝ ዘንድ ነው።

√ ቀስ ብለህ ዘምር።

√ ከመነነ በኋላ ወደዚህ ዓለም አይመለስ።

√ መነኮሳት መላእክት ምድራውያን ናቸው።

√ በአባቱ ፈቃድ የሚኖር ሕጻን ቢኖር አባቱ ባይፈቅድለት አያመንኩሱት።

√ ከመነኮሰ በኋላ የመነኩሴ ማንኛውም ገንዘብ የገዳሙ ነው።

√ ሥጋው ደሙ የተሰዋበትን ሊያርሱት ሊቆፍሩት አይገባም

√ የገዳሙን በር የሚጠብቅ ሰው ቃለ ልዝብ ይሁን።

√ መነኮሳት ሥጋዊ ጌጥ አያጊጡ።

√ አራሽ መነኮሳት በቀን ሁለት ጊዜ ማለትም ፮ ሰዓትና ፲፩ ሰዓት እንዲበሉ ተፈቅዷል። ሌሎች ግን በቀን አንድ ጊዜ ፱ ሰዓት ወይም ፲፩ ሰዓት ይበላሉ።

√ ሁለት መነኮሳት ቢጣሉና ቢመታቱ ሁለቱም 40 ቀን ከማኅበሩ ይለዩ።

√ የምንኩስና ሥራ አልቻለው ብሎ ወደ ሕዝቡ የተመለሰ በሕዝባውያን መዓርግ ይኑር። ገዳም ገብቼ ቆቤን በንሥሓ አድሼ እኖራለሁ ቢል ዕዳ የለበትም።

ስለ ቅዳሴ ይናገራል። ቅዳሴ ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይመሰገንበትም።

√ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሁሉም በጸጥታ ይቁም።

√ ማንም ቤተክርስቲያን ውስጥ አይነጋገር። ቤተክርስቲያን የጸሎት እንጂ የነገር ቦታ አይደለችምና።

√ ማንም ቢሆን ቤተክርስቲያን ውስጥ ምራቁን አይትፋ። አስቸጋሪ ነገር ካጋጠመው በመሐረቡ ወይም በነጠላው ተቀብሎ ያሻሸው

√ ካህናት በቅዳሴ መልበስ ያለባቸው ልብሰ ተክህኖ ነጭ ይሁን።

√ ቤተክርስቲያን ውስጥ ማንም ጫማውን ሳያወልቅ አይግባ።

√ ቅዳሴው ሲጀምር ያልነበረ ሰው አይቁረብ።

።

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ 13

ስለ ቁርባን ይናገራል።

።

√ ካህን ማር፣ ወተት፣ ሥጋ ወደ ምሠዊያ አያስገባ።ይህን ያደረገ ቢሆን ይሻር።

√ በየሳምንቱ እሑድ፣ ረቡዕ፣ ዓርብ እና ቅዳሜ ቁርባን ያሳርጉ።

√ ካህናት የተሳዳቢዎችን፣ የገዳዮችን፣ የሌቦችን፣ የሰካራሞችን፣ የሕግ አፍራሾችን መብዓ አይቀበሉ።

√ መጀመርያ ኤጲስ ቆጶስ ከዚያ ቀሳውስት ከዚያ ዲያቆናት ከዚያ ሕዝቡ ይቆርባሉ።

√ ማየ መቁረር (ለቆረቡት የሚሰጥ) ከአፍ እንዳይነጥብ ይጠንቀቁ። ማየ መቁረር ለቆራቢ ብቻ የሚሰጥ ነው። በቅዳሴ ጸበል ፊትን ማሻሸት መርጨት አይገባም።

ሥጋው ደሙ የሕይወታችን መሠረት ስለሆነ ሁላችንም ንሥሓ እየገባን በየጊዜው መቀበል ይገባናል።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ስለጸሎት ይናገራል።

√ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርያ ነው።

√ ጸሎት የተበደለ ድኃ ከንጉሥ እንደሚጮህ ሁሉ የሰው ልጅ ለችግሮቹ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው አቤቱታ ነው።

√ ጸሎት ሲቀርብ ባላፈው ፈጣሪን እያመሰገንን ለሚመጣው እየለመንን ኃጢአታችንን አምነን ፈጣሪን ይቅርታ እየጠየቅን መሆን አለበት።

√ ጸሎት ስድስት ክፍሎች አሉት።እኒህም:-

¶ ቀጥ ብሎ መቆም

¶ ወገብን መታጠቅ

¶ ፊትን ወደምሥራቅ ማድረግ

¶ በመስቀል ማማተብ

¶ በፍርሀት ማንበብ

¶ መስገድ

ናቸው መስቀል ማማተብ ጸሎት ልንጀምር ስንል እና ነገረ መስቀልን የሚያነሳ ቃል ስናነብ ነው። ስግደት ሦስት ዓይነት ነው። በጌታ በዓላት አንገትን ዝቅ ማድረግ (አድንኖ)፣ በእመቤታችን በዓላት ጉልበትን በርከክ አድርጎ (አስተብርኮ)፣ በሌሎች ቅዱሳን በዓላት ግንባርን መሬት አስነክቶ (ሰጊድ) መስገድ ይገባል። ጸሎት ሲጀምር ሦስት ጊዜ ሰግዶ ይጀምር። ጸሎቱን ሲጨርስም ሦስት ጊዜ ይስገድ። በቆረቡበት ቀን መስገድ አይገባም። ስግደትን የሚያነሳ ቃል ስናገኝ መስገድ ይገባል።

√ እጅን ዘርግቶ ዓይንን ወደሰማይ አንጋጦ መጸለይ ይገባል።

√ ሁሉም ሰው መዝሙረ ዳዊት አብዝቶ ሊጸልየው ይገባል። በውስጡ ምስጋና ልመና እና ተአምኖ ኃጣውዕ በብዛት አለበትና።

√ ሁልጊዜም ጠዋት መዝሙር 62ን በሠርክ መዝሙር 140ን እና በእየለቱ የሠለስቱ ደቂቅን ምስጋና መጸለይ ይገባል።

√ እሑድ ሙሉ ነቢያትን መጸለይ ይገባል። ሰኞ የሙሴን ጸሎት ንሴብሖን፣ ማክሰኞ የሙሴን ሁለተኛውን ጸሎት፣ ረቡዕ ጸሎተ ሐናን፣ ኀሙስ ጸሎተ ዕንባቆምን፣ ዓርብ ጸሎተ ኢሳይያስን፣ ቅዳሜ ጸሎተ ዮናስን መጸለይ ይገባል።

√ ማንኛውም ምእመን በቀን ቢያንስ ሰባት ጊዜ መጸለይ አለበት ሰዓታቱም:-

¶ ጸሎተ ነግህ (ጠዋት 12 ሰዓት)

¶ ከጠዋቱ ፫ ሰዓት

¶ በቀትር ፮ ሰዓት

¶ ከቀኑ ፱ ሰዓት

¶ ጸሎተ ሠርክ

¶ ማታ ፫ ሰዓት (ጸሎተ ንዋም)

¶ ሌሊት ፮ ሰዓት

ናቸው። ጠዋት የምንጸልየው ጽልመተ ሌሊትን አሳልፈህ ለዚህ ያደረስከን ብለን ነው። አዳም የተፈጠረበት ነው። ጌታም ሰውን ለማዳን በጲላጦስ ፊት የተመረመረበት ነው። ይህን እያሰብን እንጸልያለን። ፫ ሰዓት ዳንኤል የጸለየበት ጊዜ ነው። ድንግል ማርያም ብሥራት መልአክን የሰማችበት ነው፣ ሔዋን የተፈጠረችበት ነው፣ ጌታ በጲላጦስ ፊት የተገረፈበት ነው። ፮ ሰዓት አጋንንት ይሰለጥኑበታልና በእነርሱ ተንኮል እንዳንወድቅ መጸለይ ይገባል። አዳም የሳተበት፣ ጌታ የተሰቀለበት ሰዓት ነው። ፱ ሰዓት መላእክት የሰውን ምግባር የሚያሳርጉበት ነው። ጌታ ነፍሱን ከሥጋው የለየበት ነው። ሠርክ የምጽአት ምሳሌ ነው። ጌታ ወደ መቃብር የወረደበት ሰዓት ነው። ጸሎተ ንዋም ሥራኃ ሌሊትን አሳልፈህ ዕረፍተ ሌሊትን ያመጣህልን ብለን ነው። ጌታ የጸለየበት ነው። መንፈቀ ሌሊት ላይ ተነስተን እጃችንን ታጥበን እንጸልያለን። መንፈቀ ሌሊት ጌታ የተወለደበት፣ የተጠመቀበት፣ የተነሳበት፣ ዳግም ምጽአት የሚሆንበት ነው።

√ የጠዋቱን እና የሠርኩን ጸሎት በቤተክርስቲያን ይጸልዩ። በሌሎች ጊዜያት ከየትኛውም ቦታ ምእመን በቃል መጸለይ ባይችል በልቡ ይጸልይ።

√ መንገድ ለመሄድ ሲጀምሩ፣ ችግሮች ሲደርሱብን፣ እንዲደረግልን የምንፈልገው ነገር ካለ በማንኛውም ሰዓት መጸለይ ይገባል።

√ ምግብ ከመብላታችን በፊትና በኋላ መጸለይ ይገባል።

√ ምእመናን ከተወገዘ ሰው ጋር መጸለይ አይገባቸውም።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ስለ ጾም ይናገራል።

√ በሰባቱም አጽዋማት ባልና ሚስት ሩካቤ ማድረግ የለባቸውም።

√ በጾም ሥጋ፣ ቅቤ፣ ዓሣ አይበላም

√ ሰባቱ የአዋጅ አጽዋማት ለክርስቲያን ሁሉ የታዘዙ ናቸው። እኒህም:-

- ጾመ ኢየሱስ (ዐቢይ ጾም)
- ጾመ ማርያም (ፍልሰታ)
- ጾመ ሐዋርያት
- ጾመ ነቢያት
- ጾመ ነነዌ
- ጾመ ገሐድ
- ጾመ ድኅነት (ዓርብ ረቡዕ)

ናቸው። የነቢያት ጾም በአራቱም ዓመት ህዳር 15 ይጀምራል። ጾመ ነቢያት መባሉ የነቢያት ትንቢት ስለተፈጸመበት ነው። በሦስቱ ዓመት ታኅሣሥ 29 ልደት ይውላል። በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሥ 28 ይውላል። ጾሙ የሚጀምርበት ዕለት ግን የአራቱም ዓመት ህዳር 15 ነው። ዓርብ እና ረቡዕ በበዓለ ፶ አይጾሙም። ልደት እና ጥምቀት ከዋለባቸውም አይጾሙም። የጥምቀት እና የልደት ዋዜማ ይጾማል። ስሙም ገሐድ(ጋድ) ይባላል። ሰኞ ጥምቀት ሲውል ቅዳሜ እና እሑድ ሁለት ቀን ይጾማል የሚሉ አሉ። ፍትሐ ነገሥት ግን ስለማይል ጥምቀት ወይም ልደት ሰኞ ቢውል እንኳ ገሐድ እሑድ ብቻ ነው። የሐዋርያት ጾም መጨረሻው የጴጥሮስ ወጳውሎስ ሐምሌ ፭ ነዉ ። ጾመ ማርያም ከነሐሴ ፩ እስከ ነሐሴ ፲፭ የሚጾመው ነው።

√ በጾም ሥርየተ ኃጢኣት፣ ሰማያዊ ዋጋ ይገኛል።

√ ጾም ማለት ከምግብ መከልከል ማለት ነው።

√ ጾም የፍትወት ጾርን ያርቃል።

√ ጾም ሥጋን ለነፍስ ለማስገዛት ትረዳለች።

√ ከአዋጅ ጾም በተጨማሪ የሚጾም ሰውም ቢኖር ዋጋው ይበዛለታል።

√ ከቅዳም ስዑር ውጭ ሌላ ቅዳሜ አይጾምም። እሑድም አይጾምም።

√ በጾማችን መላእክትን እንመስላለን።

√ የሚጾም ሰው የረኀብን የጥምን ጾር ያውቅ ዘንድ እና ለተራቡትና ለተጠሙት ይራራላቸው ዘንድ ነው።

√ በሰሙነ ሕማማት ኀብስትና ጨው ብቻ ይብሉ።

√ በሰሙነ ሕማማት የቻለ ዓርብና ቅዳሜን ይጹም። ያልቻለ ቅዳሜን ጹሞ ያክፍል።

√ የትንሳኤ እሑድ ዶሮ ሳይጮህ አይብሉ (፲ ሰዓት አካባቢ ይብሉ)

√ ታሞ ካልሆነ በቀር ካህን ሆኖ ዐቢይ ጾምን እና ዓርብ ረቡዕን የማይጾም ይሻር። ምእመንም ይለይ።

√ ከቅዳም ስዑር ውጭ ቅዳሜ እና እሑድ ሲጾም የተገኘ ካህን ይሻር።

√ በዓቢይ ጾም የሰማዕታት የቅዱሳን በዓል ቢውል ሰኞ ማክሰኞ ቢውል ባለፈው እሑድ ቅዳሜ ይከበር። ረቡዕ ቢውል ወይ ባለፈው እሑድ ቅዳሜ ወይም በሚመጣው እሑድ ቅዳሜ ያክብሩ። ሐሙስ ዓርብ ቢውል በሚመጣው እሑድ ቅዳሜ ያክብሩ።

√ ካህን በዐቢይ ጾም እና በዓርብ ረቡዕ ወይን ሊጠጣ አይገባም።

√ የጥምቀትና የልደት ቁርባን በሌሊት ይሁን።

√ ጾም ከምግብ መከልከል ብቻ አይደለም ልብን ንጹሕ ማድረግም ነው እንጂ። (እስከ ዕለተ ሞታችን ከኃጢኣት መከልከል ይገባል። ቅዱስ ያሬድ ዓይን ክፉ ከማየት ጆሮ ክፉ ከመስማት ይጹም እንዳለ። ዓይን ይጹም ዕዝንኒ ይጹም እምሰሚዐ ኅሱም)

√ በዐቢይ ጾም ጥምቀት (ክርስትና)፣ ክህነት አይሰጥም። ፍትሐት ግን ይቻላል። ሞት የሚያሰጋው ተጠማቂ ካለ ግን እንዲጠመቅ ሥርዓት ተሠርቷል።

√ በትንሳኤ ግንዘት አይገባም። ማዘን ማልቀስም አይገባም።

{የጽጌ ጾም፣ የጳጉሜን ጾም የፈቃድ ጾም ነው። ስለዚህ የፈለገ መጾም ያልፈለገ መብላት ይችላል}

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ስለ ምጽዋት ይናገራል።

√ ምጽዋት ስርየተ ኃጢኣትን ታሰጣለች። ከክፉ ነገርም ታድናለች።

√ ምጽዋት ከሰጡት ሰው ምላሽ ሳይሹ የሚሰጧት ስጦታ ናት።

√ በምጽዋት ሰው ፈጣሪውን ይመስላል።

√ ባዕለ ጸጎች ብዙ ምጽዋት ይጠበቅባቸዋል።

√ እስረኞችን እናንተ እንደታሰራችሁ አድርጋችሁ አስቧቸው።

√ እንግዳ መቀበል ቁጥሩ ከምጽዋት ነው።

√ ምጽዋት በሁለት ይከፈላል። እኒህም በግልጥ የሚሰጥና በስውር የሚሰጥ ተብለው ይከፈላሉ። በግልጥ የሚሰጥ አስራት፣ በኩራት፣ ስለት ነው። ሌላው ለተቸገረ የሚሰጠው በስውር ይሰጣል።

√ ምጽዋትን በጣም ለተቸገረ ሰው ሊሰጧት ይገባል። መጀመርያ ለዘመድ፣ ከዚያ ለምእመናን ከዚያ ሃይማኖት ለሌላቸው ይሁን።

√ ዘመን እንዳለን መልካም እንስራበት።

√ ያልተቸገሩ ሰዎች ምጽዋት መቀበል አይገባቸውም።

√ እየተቻለው ምጽዋት የማይሰጥ ሰው እንደ ከሃዲ ነው።

√ ከክፉ ሰዎች ምጽዋትን አትቀበሉ።

√ ገንዘብ የቀሙ ሰዎች ለባለቤቱ አምስት እጥፍ አድርገው ይመልሱ።

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አስራ #ሰባት

በቤተክርስቲያን ገንዘብና በምጽዋት ላይ ስለሚሾሙ ሰዎች ይናገራል።

√ በቤተክርስቲያን ገንዘብ ሁሉ ኤጲስ ቆጶስ ያዝዝበት። የተቸገሩ ሰዎችንም ይርዳበት።

√ የቤተክርስቲያንን ገንዘብ የሸጠ እና የገዛ ለቤተክርስቲያን ይመልስ። እምቢ ካሉ ኤጲስ ቆጶስ እጥፍ ያስከፍላቸው።

√ የታመሙ፣ የተቸገሩ ሰዎችን እና እንግዶችን የሚረዳ ሰው ኤጲስ ቆጶሱ ይሾማል። ገንዘብ ቢያንስ የተሾመው ለተቸገሩት ከምእመናን ይለምንላቸው።

√ ቤተክርስቲያን አግብተው ሊጸልዩባቸው የሚገቡ ወይን፣ በለስ፣ ሮማን፣ ዘይት፣ ሙዝ፣ እንኮይ፣ ኮክ፣ ጽጌረዳ፣ ሽቱ የመሳሰሉት ናቸው። ወደ ቤተክርስቲያን ሊያገቧቸው የማይገቡ ሽንኩርት፣ ዱባ፣ ቅል፣ ሾላ እና የመሳሰሉት ናቸው።

√ ምእመናን የሚበላውን በልተው እግዚአብሔርን ያመስግኑ።

√ ከቤተክርስቲያን ገንዘብ ለጳጳሱ አራት እጅ፣ ለቄሱ ሦስት እጅ፣ ለዲያቆኑ ሁለት እጅ፣ ከዚያ በታች ላሉት አንድ አንድ እጅ ይድረሳቸው።

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አስራ #ስምንት

ስለ ዓሥራት፣ ስለ በኩራት፣ ስለ ስለት እና ስለጉልት ይናገራል።

√ ሰርታችሁ ካገኛችሁት ከአስር አንድ ለቤተክርስቲያን ስጡ።

√ ስለት ከክፉ ለመዳን ወይም መልካም ነገርን በመሻት ሰው ከፈጣሪ ጋር በገንዘቡ ወይም በራሱ ወይም በልጁ የሚማማላት መሐላ ናት።

√ መከራ ባገኘው ጊዜ ተስሎ በድኅነቱ ወይም በሌላ ምክንያት ስለቱን መፈጸም ለማይችል ሰው ካህን ሁኔታውን መርምሮ ይወስንለት።

√ ከብት ተስሎ በኋላ ከብቱን ማስቀረት ቢወድ ካህኑ የከብቱን ዋጋ ሳያዳላ ወስኖ ይቀበለው።

√ በአባቷ ቤት እያለች አባቷ ሳይፈቅድ የተሳለች ሴት ብትኖር አባቷ ስለቷን አላስፈጽምም ቢል በደል የለበትም። እርሷም ስለቷን ባለመፈጸሟ በደል አይሆንባትም። ባሏ ወይም አባቷ ስለቷን ሰምቶ ቸል ብሎ በኋላ ግን ቢቃወም ግን በደሉ በእርሱ ይሆናል።

√ ለተቸገረ ሰው ጉልት መጎለት በወዲያኛው ዓለም ዋጋን ያስገኛል።

√ የሚጎለት ጉልት እንደ ቤት እንደ እርሻ በታ ያለ የማይንቀሳቀስ ሊሆን ይገባል።

√ በኩራት የሚባለው የእናቱን ማኅጸን የፈታ የመጀመሪያ ልጅ ነው። የሰውም የእንስሳትም የሌላውም ነው። ያ የእግዚአብሔር ነው።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ስለ ቅዱሳት በዓላት ይናገራል።

√ ሰባቱ የጌታ ዐበይት በዓላት የሚባሉት:-

- ትስብእት (መጋቢት 29)
- ልደት (ታኅሣሥ 29)
- ጥምቀት (ጥር 11)
- ሆሣዕና
- ትንሣኤ
- ዕርገት
- ጰራቅሊጦስ

ናቸው። {ደብረ ታቦርን (ነሐሴ 13) እና ስቅለትን ጨምረው ቆጥረው ዘጠኝ የሚያደርጓቸውም አሉ}።

√ ዘጠኙ ንዑሳን የጌታ በዓላት የሚባሉት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

- መስከረም 17/መጋቢት 10
- ስብከት
- ብርሃን
- ኖላዊ
- ጌና (ታኅሣሥ 28)
- ልደተ ስምዖን (የካቲት 8)
- ደብረ ዘይት
- ቃና ዘገሊላ
- ግዝረት (ጥር 6)

√ እሑድ ቅዳሜ እና በጌታ በዓላት ሥራ ሊሰሩ አይገባም። ስግደትም ሊሰገድባቸው አይገባም።

√ እሑድ ቀን አያፋርዱ አያሟግቱ

√ በዓላት የደስታ ቀኖች ናቸው።

√ ሁልጊዜም ወደቤተክርስቲያን ተሰብሰቡ። ይልቁንም በሰንበትና እሑድ ኑ።

√ ረብኅ ጥቅም የሌለው ነገር አትናገሩ።

√ ባሮችን (የቤት ሠራተኞቻችሁንም) በእለተ ስንበት ቅዳሜ እና እሑድ ፍቀዱላቸውና ወደቤተክርስቲያን ሄደው ነገረ ሃይማኖትን እንዲማሩ አድርጉ።

√ ትንሣኤን ከእሑድ ውጪ አታክብሩ።

√ የትንሣኤ የልደት እና የጥምቀት ቁርባን ሌሊት 10 ሰዓት ይሁን። በበዓለ ፶ እና ቅዳሜ ቁርባን ጠዋት 3 ሰዓት ይሁን። የጸሎተ ሐሙስ በሠርክ ይሁን። በሰባቱ አጽዋማት በዘጠኝ ሰዓት ይሁን። እሑድ ጠዋት አንድ ሰዓት ይሁን።

√ በትንሣኤ የሚጾም ሰው ኃጥዕ ነውና ኵነኔ ይገባዋል።

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሐያ

ስለሰማዕታት ይናገራል።

√ ሰማዕታት በእናንተ ዘንድ የከበሩ ይሁኑ።

√ ሰማዕታትን ከእስር ለማስፈታት ገንዘቡን የሚሰጥ ሰው ንዑድ ክቡር ነው።

√ ሰማዕታትን እየረዳህ መከራ ቢያገኝህ ሰማያዊ ዋጋህ ይበዛል።

√ በሃይማኖታቸው ምክንያት ከሀገር ሀገር የሚሳደዱትን ተቀበሏቸው አክብሯቸው።

√ ከእግዚአብሔር ይልቅ ራሱን የወደደ ሰው ይቅርታን አያገኝም።

√ ይህንን ዓለም እና ክብሩን አንውደደው።

√ ለሌሎች የጥፋት ምክንያት አንሁን።

√ በመከራ ብንጨነቅም ሃይማኖታችንን አንለውጥ።

√ ተአምራትን አይቶ በመጨረሻው ሰዓት ያመነን ሰው ሳይጠመቅ ቢገድሉት ደሙ ጥምቀት ይሆነዋል

√ ፈርቶ ሃይማኖቱን ከካደ በኋላ እንደገና ንሥሓ ገብቶ ቢመለስ ቀድሞ ካህን ከነበረ በክህነቱ ይቀጥል። ምእመን ከሆን አስቀድሶ ይቁረብ።

√ የሰማዕታትን በዓል ሰማዕት በሆኑበት ዕለት ያክብሩት። በዚህ ቀን ገድላቸውም ይነበብ። የሰማዕታትን አጽም በቤተክርስቲያን ያኑሩ።ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ስለድውያን ይናገራል።

√ የታመመ ሰው ቢኖሩ ይጸልዩለት ዘንድ ቀሳውስትን ይጥራ።

√ ቅቤ የሚቀባ ሰው ለራሱ ሳይተርፍ ሌላውን እንዳይቀባ የሚጸልይም ሰው ራሱን ሳያድን ሌላውን አያድንም።

√ ጌታ ብታመም ጠይቃችሁኛልና ብሎ ለታመመ ሰው እርዳታ ያደረገውን ሰው በምጽአት ጊዜ ወደእኔ ና ይለዋል።

#ፍትሐ #ነገሥት #ክፍል ፳፪

ስለ ሙታን ይናገራል።

√ መዋቲ ሕያውን መሰናበቱ እኔ እንደናንተ ነበርኩ እናንተም እንደእኔ ትሆናላችሁ ብሎ ነው።

√ ለሞቱ ሰዎች ጸልዩላቸው።

√ ሴት ልጅ በወሊድ ምክንያት ብትሞት ወይም በወር አበባዋ ጊዜ ብትሞት አጥበው በሌላ ልብስ ገንዘው ይቀበሯት።

√ ከመገነዙ በፊት ሟችን ማጠብ ይገባል።

√ ሟቹ ካህን ቢሆን ከመቅደስ አግብተው ያሰግዱት። ሟቹ ህዝባዊ ቢሆን ከቅኔ ማኅሌቱ ከቅድስቱ አግብተው ያሰግዱት።

√ ወንድ ወንዱ በአንድ፣ ሴት ሴት በአንድ፣ ሕጻናት በአንድ አካባቢ ሊቀበሩ ይገባል።

√ ሟቹ በሞተበት ዕለት ሊያስቆርቡለት (ሊያስቀድሱለት)/ይገባል። ከዚያ በሣልስቱ፣ ከዚያ በሰባቱ፣ ከዚያ በአስራ ሁለቱ፣ ከዚያ በሠላሳ፣ ከዚያ በአርባ፣ ከዚያ በመንፈቅ ያስቆርቡላቸው። በሣልስት ቢታጎል በሦስተኛው ሣልስ በዘጠኝ፣ በሰባት ቢታጎል በአስራ አራት፣ በሠላሳ ቢታጎል በስልሳ፣ በአርባ ባታጎል በሰማንያ፣ በመንፈቅ ቢታጎል በዐመቱ ያስቆርቡለት። ከታቸለ ግን ከሞተ ጀምሮ አርባውን ቀን ሁሉ ያስቆርቡለት።

√ ለመቃብር ቆፋሪዎች ኤጲስ ቆጶስ ከቤተክርስቲያን ዋጋቸውን ይስጣቸው።

√ ሰው ሲሞት በጣም ማዘን፣ ራስን መላጨት፣ ልብስን መቅደድ አይገባም።

ከአንቀጽ ፩ እስከ አንቀጽ ፳፪ ፍትሕ መንፈሳዊ ይባላል። ከቀጣይ ክፍሎች ጀምረን ማለትም ከአንቀጽ ፳፫ እስከ አንቀጽ ፶፩ የምናየው ፍትሕ ሥጋዊ ይባላል።

ናሁ ተፈጸመ ፍትሕ መንፈሳዊ

በሰላመ እግዚአብሔር ።

ስለ ልብስ፣ ስለ ምግብ፣ ስለ ቤት፣ ስለ ተግባረ እድ ይናገራል።

√ ጥሬ ሥጋ እና ደም መብላት አይገባም።

√ ሞቶ ያደረ፣ የአውሬ ትራፊ፣ ለጣዖት የተሠዋ አይበላም።

√ እየተጠራጠሩ መብላት ኃጢአት ነው።

√ አእምሮን የሚያጠፉ፣ ሰውነትን የሚጎዱ ነገሮችን መብላት አይገባም።

√ መርዝ ያላቸው ፍጥረታትን፣ መርዝ የሚበሉ አራዊትን መብላት አይገባም።

√ ለታመመ ሰው ግን ደዌውን የሚያድንለት ከሆነ ማናቸውንም ነገር እንዲበላ ይፈቀድለታል።

√ የሚበላ የማይበላን፣ የማይበላ የሚበላን አይንቀፍ።

√ ከማያምኑት ሰዎች ምግብ አቅርበው ብሉ ቢሏችሁ ባርካችሁ ብሉት። ነገር ግን ለይተው ለጣዖት የታረደ ነዉ ካሏችሁ አትብሉ።

√ ከጥጋብና ከስካር ተጠበቁ።

√ አንድ ዓይነት ቀለም ያለው ልብስ መልበስ ይገባል። ሐረግ የተሳበበት ዛፍ እና የተለያየ ቅርጽ የተቀረጸበትን መልበስ አይገባም።

√ በጣት ቀለበት ማድረግ አይገባም {በሰርግ ጊዜ በተክሊል የሚደረገው እንኳ አንድ ሰፊ ቀለበት ነው። የሁለቱንም ጣት በአንድ ማስገባት የሚችል ይሆናል። ካልበቃ ተራ በተራ ያንኑ አንዱን ቀለበት ያደርጉታል። የተክሊል ሥርዓቱ እንዳለቀ እንደ ካባው ሁሉ ለቤተክርስቲያኑ ይመለሳል}

√ ሴቶች በወርቅ የተጌጠ በወርቅ የተነበነበ አይልበሱ (ሐተታ ሴቶች ትእቢተኞች ናቸውና ይህን ሲለብሱ መሬት ይለቃሉና)።

√ ካህናት የወታደር ልብስ አይልበሱ።

√ ልብስ መልበስ ዕርቃንን ለመሸፈን ከውርጭ ከቃጠሎ ለመዳን ነው።

√ ክርስቲያን ሊሰራቸው የማይገቡ የተከለከሉ የሥራ ዓይነቶች:-

- ጥንቆላ
- ጣዖት መስራት
- ዘፋኝነት
- ተውኔት

ናቸው። ከተጠመቀ በኋላ እኒህን ሲሰራ የተገኘ ክርስቲያን እንዲተው ይንገሩት። ካልተመለሰ አውግዘው ይለዩት። ክርስቲያን ሊሰራቸው ከሚገቡ ሥራዎች ጥቂቶቹ:-

- ልብስ መስራት
- ሕንጻ ማነጽ
- ሐኪምነት

- ግብርና
- ንግድ

ንግድ ከአንዱ ሀገር ያለውን ወደ አንዱ ሀገር ለመውሰድ በግድ ያስፈልጋል።

።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

ስለ ጋብቻ፣ ስለ እጮኝነት ይናገራል።

√ ጋብቻ ሦስት ዓላማዎች አሉት።

- ብዙ ተባዙ ያለውን ሕግ ለመፈጸም።
- በዝሙት ላለመውደቅ
- ለመረዳዳት

√ ወንድ ከሴት ሄዶ ማጨት ይገባል። ሽማግሌ የሚልክ ወንድ ነው። አዳም ሔዋንን በተጣላት ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ሊያስታርቃቸው ሄደህ ታረቅ አለው። እርሷ ትምጣ እንጂ እኔ አልሄድም አለው። አኮ መፍትው ትሑር ብእሲት ኀበ ብእሲሃ አላ መፍትው ይሑር ብእሲ ኀበ ብእሲቱ ብሎታልና።

።

√ በነገረ ሥጋዌ ቃል የሙሽራ ሥጋ የሙሽሪት ምሳሌ ነው። ባዕድ መለኮት ከባዕድ ሥጋ ጋር ተዋሕዷል። ባዕድ ከባዕድ ይጋባ ሲል ነው። ባዕል መለኮት ከነዳይ ሥጋ ተዋሕዷል። ባዕለ ጸጋ ከድኃ መጋባት እንደሚችሉ ሲነግረን ነው።

√ ሕግ ሥርዓት ከማፍረስ የሚያደርስ የፈቲው ጾር ቢጸና ማግባት ይገባል።

√ ሰው ንጽሕ ጠብቆ ከሴት ርቆ መኖር ባይቻለው ሚስት አግብቶ ይኑር። በፍትወት ከመቃጠል ማግባት መልካም ነውና።

√ አንድ ሰው በድንግልና እኖራለሁ ብሎ ከተሳለ በኋላ ቢያገባ ሁለተኛ ሚስት እንዳገባ ይቆጠራል::

√ ሁለተኛ ለሚያገባ እና ድንግልናውን ላልጠበቀ ሰው ተክሊል አይደረግለትም። ማግባት ቢፈልግ በጸሎተ መዓስባን በቁርባን ያገባል።

√ ሁለተኛ ያገባ ካህን ወይም ከሚስቱ ውጪ ከሌላ ሴት የደረሰ ካህን ከክህነቱ ይሻራል።

√ ቅዱሳን እነ አብርሃም፣ እነ ይስሐቅ ቢያገቡ ጋብቻን ለዝሙት ፈልገውት ሳይሆን ዘር ለመተካት ነበር።

√ ሚስትህ ጽንሷ ከታወቀ በኋላ ማለትም ጽንስ ከገፋ ሆድ ከሰፋ በኋላ ግንኙነት ማድረግ አይገባም።

√ ማንኛውም ሰው ራሱ ሄዶ ማጨት ይገባዋል። እርሱ ባይሄድ ደብዳቤ ሰዶ፣ ደብዳቤ ባይልክ ሽማግሌ ልኮ ማጨት ይገባዋል። አሳዳጊዎቹ ወይም ወላጆቹ ማጫ መስጠት ይገባቸዋል።

√ ጋብቻ የሚከለከልባቸው ዝምድናዎች አራት ናቸው እነዚህም:-

- የሥጋ ዝምድና
- መንፈሳዊ ዝምድና
- የአሳዳጊ ዝምድና
- የጋብቻ ዝምድና

ናቸው።የጋብቻ ዝምድናን ቀጣይ ክፍል ላይ ክፍል 18 እናየዋለን። የሥጋ ዝምድና የሚባለው የሚጋቡት ሰዎች በእናት ወይም በአባት በኩል ሲቆጠሩ እስከ ሰባት ባለው ተመሳሳይ አያት ካላቸው አይጋቡም። በስምንተኛው ግን መጋባት ይችላሉ። መንፈሳዊ ዝምድና የሚባለው በክርስትና አባት እና በክርስትና እናት የሚቆጠረው ዝምድና ነው። ይህም ክርስትና አንሺ ከተነሺ አይጋቡም። ባል የሚስቱን ክርስትና ልጅ ሚስት የባሏን ክርስትና ልጅ ማግባት አይፈቀድም። የአንሽ እናት አባት ከተነሺ እናት አባት አይጋቡም። የአንሺ ወንድም እህት ከተነሽ ወንድም እህት አይጋቡም። የአንሺ

ልጅ ከተነሺ ልጅ አይጋቡም። የአንሺ የልጅ ልጅ ከተነሺ የልጅ ልጅ አይጋቡም። የአንሺ የእንጀራ ልጅ (የሚስት ልጅ) ከተነሽ የእንጀራ ልጅ አይጋቡ። ባጭሩ ሚስት ከሌላ የወለደቻትን ልጇን ባሏ ክርስትና ላነሳው ልጅ ማጋባት አይገባም።

√ ሥጋዊ ዝምድናን እያወቀ ተደፋፍሮ ያፈረሰ ቢኖር ይፋታና ቀኖናውን ጨርሶ ሌላ ያግባ። መንፈሳዊ ዝምድናን እያወቀ ተደፋፍሮ ያፈረሰ ቢኖር ይፋታና ይመንኩስ።

√ አንድ ሰው አንድን ልጅ በማደጎ ቢወስደው እና ቢያሳድገው አዳጊና አሳዳጊ መጋባት አይገባቸውም። የአዳጊ እናት አባት አያት ከአሳዳጊ እናት አባት እያት መጋባት አይገባቸውም። የአዳጊ አክስት አጎት ከአሳዳጊ አክስት አጎት መጋባት አይገባቸውም።

{ይህን ሁሉ ባለማወቅ ስንተገብረው ኖረን ይሆናል። ስለዚህ ባለማወቅ ያጠፋነውን እግዚአብሔር ይቅር ይበለን እና ወደፊት ግን ይህንን አውቀን ጥንቃቄ እንድናደርግ ለማሳሰብ ነው የጻፍኩት። የጋብቻ ዝምድና እና ሌሎች ጋብቻን በተመለከተ በቀጣዩ ክፍል በሰፊው እጽፋለሁ። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ሰፊ ስለሆነ እኔም በሁለት ክፍል አቀርበዋለሁ}ስለ ጋብቻ የቀጠለ

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ 24 ፪

√ ባል ለሚስቱ የሚገባውን ፍቅር ያድርግላት፣ ሚስትም ለባሏ የሚገባውን ፍቅር ታድርግለት።

√ መተጫጨት ጥቅሙ ጋብቻ በፍጹም ምክር ፈቃድ ይፈጸም ዘንድ ነው። መልካቸውን፣ ሥራቸውን፣ ጠባያቸውን የሚተዋወቁበት ነው። (እንጂ በቃላት የሚደላለሉበት አይደለም)። እርሱም ሌላ ሳያውቅ እሷም ሌላ ሳታውቅ የተጋቡ እንደሆነ ፍቅራቸው ይጸናል።

√ ሴት ራሷን ችላ የምትኖር ከሆነ በራሷ ፈቃድ የፈለገችውን ማግባት ትችላለች።

√ ከሙሽሮቹ አንዱ ድንግል አንዱ ድንግል ያልሆነ ቢሆኑ ድንግል ለሆነው ተክሊል ያድርጉለት። ላልሆነው አያድርጉለት።

√ ከስልሳ (60) ዓመት በላይ የሆናት ሴት ልታገባ አይገባትም።

√ ወንድ ሚስቱ ከሞተች በኋላ ከዓመት በኋላ ማግባት ይችላል። ሴትም ባሏ ከሞተ በኋላ አስር ወር ቆይታ ማግባት ትችላለች። ከዚያ በፊት ግን ሁለቱም ማግባት አልተፈቀደላቸውም።

√ በሃይማኖት የማይመስለንን ማግባት አይገባም።

√ የጋብቻ ዝምድናን ማፍረስ አይገባም።

√ ወንድም የወንድሙን ሚስት እኅት፣ አጎት የወንድሙን ልጅ ሚስት እኅት፣ ወንድም የወንድሙን ሚስት እኅት፣ አጎት የወንድሙን ልጅ ሚስት አያት፣ ባል የሚስቱን ዘመዶች፣ ልጅ የአባቱን ሚስት አያገባም። ሮቤል ከአባቱ ዕቁባት ደርሶ ተረግሟልና።

√ የልጅ ልጅ የአያቱን ሚስት፣ ልጅ የአባቱን ሚስት እኅት፣ የልጅ ልጅ የአያቱን ሚስት እኅት፣ ልጅ የአባቱን ሚስት አያት፣ የልጅ ልጅ የአያቱን ሚስት አያት፣ ወንድም የወንድሙን ሚስት፣ አጎት የወንድሙን ልጅ ሚስት ማግባት አይገባቸውም።

√ አባት የልጁን ሚስት እኅት፣ አያት የልጅ ልጁን ሚስት እኅት፣ አባት የልጁን ሚስት እናት፣ አያት የልጅ ልጁን ሚስት እናት፣ አባት የልጁን ሚስት አያት፣ አያት የልጅ ልጁን ሚስት አያት ማግባት አይገባቸውም።

√ ከእናቱ ማኅጸን ሕጽው (ጃንደረባ) ሆኖ የተወለደ ቢኖር አያግባ።

√ ፍናፍንታም ማግባት አይገባውም። ፍናፍንታም ማለት የሴትም የወንድም መሽኛ ያለው ማለት ነው። ሴት ቢያጋቡት ወንድ አምጡልኝ ይላል፣ ወንድ ቢያጋቡት ሴት አምጡልኝ ሊል ይችላልና።

√ የተሰለበ ሰው እና አካልን የሚቆራርጥ ደዌ ሥጋ ያለባቸው ሰዎች ሊያገቡ አይገባም።

√ በሁለተኛ እና በሦስተኛ ጋብቻ ተክሊል ማድረግ አይገባም።

√ ሰባት ዓመት ላልሞላው ሕጻን ማጨት አይገባም። አዳም ከሰባት ቀን አስቀድሞ ሔዋንን አላገኘምና።

√ አጭቶ ለማግባት ቀን ያልወሰነ ሰው በሀገር ያለ ቢሆን ሁለት ዓመት ይጠብቁት። ሩቅ ሀገር የሄደ ቢሆን ሦስት ዓመት መጠበቅ ይገባል። አራት ከሆነ በኋላ ግን ሌላ ማግባት ይቻላል።

√ አባትም እናትም አሳዳጊም የሌላቸው ሰዎች ቢኖሩ 15 ዓመት ከሞላቸው በኋላ በራሳቸው ፈቃድ መጋባት ይችላሉ።

√ ወንድ 20 ዓመት ሳይሞላው ሴት 12 ዓመት ሳይሞላት ማግባት አይገባቸውም።

√ ካህን ሚስቱ ብትሞትና ሌላ ቢያገባ ከክህነቱ ይሻራል። ሦስተኛ ካገባ እርኩስ ይባላል። ምእመን ሚስቱ ብትሞትበት ሌላ ያገባል። ሁለተኛዋም ብትሞትበት ሦስተኛ ያገባል። ከሦስተኛ በላይ ማግባት ግን አልተፈቀደም።

√ በጾም ወቅት ሩካቤ (ግንኙነት) ማድረግ አይገባም።

√ በአራስነቷ እና በወር አበባዋ ወቅት ከሚስት ጋር ሩካቤ ማድረግ አይገባም። የአባለ ዘርዕ በሽታ ይይዛልና።

√ ከሴት ማኅጸን ውጭ ዘርን ማፍሰስ አይገባም። ጋብቻ ልጅ ለመውለድ እንጂ ለዝሙት አልተሰጠምና።

√ ጋብቻንም ሩካቤንም ርኩስ ነው ማለት አይገባም።

√ ሴት በወር አበባዋ ወቅት ወደ ቤተክርስቲያን አትግባ። ከወለደች በኋላም ወንድ ከወለደች እስከ አርባ ቀን ሴት ከወለደች እስከ ሰማንያ ቀን አትግባ።

√ አዋላጆች ወንድ ካዋለዱ እስከ ሃያ ቀን ሴት ካዋለዱ እስከ አርባ ቀን አይቁረቡ

√ ባል ሚስቱ ስትሰስን አይቶ ካልፈታት ሁለቱም ከምእመናን ይለዩ።

√ ከጋብቻ በኋላ አንዱ የአንዱን ፈቃድ አልፈጽምም ቢሉ ጋብቻ ይፈርሳል።

√ ከጋብቻም በኋላ ሩካቤን አዘውትሮ መፈጸም አይገባም። ሴሰኝነት ነውና።

√ በወንዱ አባለ ዘርዕ ወይም በሴቷ ማኅጸን ምክንያት ሩካቤ ማድረግ የማይቻል ከሆነ (የሩካቤ አለመጣጣም) ሦስት ዓመት ቆይቶ መፋታት ይቻላል።

√ መሸታ ቤት ዲያብሎስ ምእመናንን የሚያጠምድበት ቤት ነው።

√ ሕግ በማይከለክለው ምክንያት ባል ወይም ሚስት ልፋታ ካሉ ቄሱ እንዳይፋቱ ይምከራቸው ይለምናቸው። ቄሱን እምቢ ካሉ ጳጳሱ ይምከራቸው ይለምናቸው። ጳጳሱንም እምቢ ካሉ እምቢ የተባለው አካል ሌላ ቢያገባ በደል የለበትም።

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ 25

ስለ ዕቁባት ይናገራል።

√ በሐዲስ ኪዳን ላለን ለእኛ ዕቁባት መያዝ አይገባም/አይፈቀድም። ዕቁባት ማኖር ይስማ ይልማ ብለው የሚሰሩት ዝሙት ነውና።

√ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደ አሁኑ ሥርዐት አልጸናም ነበርና እነ ዳዊት እነ ሰሎሞን ብዙ ዕቁባቶች ነበሯቸው።

√ በሐዲስ ኪዳን ግን እንደዚህ የለም። ጌታ አገልጋዩን ሴት ነጻ አውጥቶ ማግባት ይችላል

ስለ ስጦታ ይናገራል።

√ ገንዘብ ለሌለው ለድኃ የሚሰጡት ስጦታ ምጽዋት ይባላል። ገንዘብ ላለው ሰው በውዴታ በፍቅር የሚሰጡት ስጦታ ሀብት ይባላል።

√ ስጦታ ነውር ቢገኝበት ይመለሳል። (ለምሳሌ የተሰረቀን ነገር ስጦታ አድርገው ቢሰጧችሁ ይመለሳል)።

√ ሰጪ ገንዘቡን ከሰጠ በኋላ ተቀባይም ገንዘቡን ከተቀበለ በኋላ ለተቀባይ በገንዘቡ ማዘዝ መሰልጠን ይገባዋል።

√ ስጦታ የሚሰጠው ሰው ለአካለ መጠን ያልደረሰ፣ አእምሮው ያልተደላደለ ሕጻን ቢሆን ስጦታውን መቀበል አይገባም።

።።።።።።።።።።

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሃያ #ሰባት

ስለ ብድር ይናገራል።

√ ብድርም ቁጥሩ ከምጽዋት ወገን ነው። በረኀብ ዘመን ማበደር ከምጽዋት ቁጥር ነውና።

√ አራጣ መብላት ትልቅ ኃጢአት ስለሆነ አይገባም።

√ የሚከፍለውን እስኪያገኝ ድረስ አበዳሪ ተበዳሪን መታገሥ ይገባዋል።

√ ገንዘብህን ከተበደረህ ሰው ጠዋት ማታ እየሄድክ አታስጨንቀው።

√ ስታበድር በመያዣ፣ በደብዳቤ፣ ወይም በዋስ መሆን አለበት።

√ ተበዳሪ አበዳሪውን ቢክድና ቢምል በምስክሮች ከተረጋገጠበት እጥፍ ይከፍላል።

√ በመያዣ ያበደረ ሰው መያዣው ቢጠፋበት መያዣውን የመሰለ ይተካ። መያዣው ከብድሩ እኩል ቢሆን ብድሩ ይቀራል።

√ እስከ ሠላሳ ዓመት ዝም ብሎ ቆይቶ ከዚያ በኋላ ገንዘቤን ስጡኝ ቢል ሊሰጠው አይገባም። ከሠላሳ ዓመት በኋላ ከሠላሳ ዓመት በፊት ያለ የዕዳ ፍርድ ተፈጻሚ አይሆንም።

√ አባት በልጁ፣ ልጅ በአባቱ ብድር አይጠየቅም። ይኸውም እርሱ አዞት የተበደረ ካልሆነ ነው።

√ ወንድም በወንድሙ፣ ልጅ በአባቱ ደም መያዝ አይገባውም። አብሮ የመከረ አብሮ የገደለ ቢሆን ነው እንጂ

√ ዋስ የሚሆን ሰው ራሱን የቻለ አዋቂ መሆን አለበት።

√ ይከፍላል ለማይሉት ሰው ገንዘብ መስጠት እንጂ መዋስ አይገባም።

√ ካህን ለማንም መዋስ አይገባውም።

:::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሃያ #ስምንት

ስለ ውሰት ይናገራል።

√ ውሰት በታወቀ ሰዓትና በታ ዋጋ ሳይቀበሉ ወይም ሳይሰጡ ጥቅም የሚገኝበትን ገንዘብ መዋስ ወይም ማዋስ ነው።

√ እንስሳ የተዋሰ ቢኖር እና ከተፈቀደለት በታና ጊዜ በላይ አቆይቶ ሳለ ቢሞትበት የተዋሰው የእንስሳውን ዋጋ ይከፍላል። ቸል ብሎ ከገደል አፋፍ እያየው ገደል ገብቶ ቢሞት ተጠያቂ ነው። ካዋሰው ሰው ጋር ሳሉ ከሆነ ግን አይጠየቅም።

√ የተዋሰ ሰው በገንዘብ ከሆነ የተዋሰ ከተዋሰበት ቦታ በላይ እንዲሁም ጊዜ ቢጠቀምበት ጨምሮ ይክፈል።

√ ያዋሰ ሰው በፈለገው ጊዜ መልስልኝ ማለት ይችላል።

ስለ አደራ የአደራን ነገር ይናገራል።

√ አደራ አስጠባቂ ከጠባቂ ዘንድ አምኖ የሚያኖራት ገንዘብ ናት።

√ ተሰርቆ የመጣን ገንዘብ ወይም ንብረት እያወቀ በአደራ ለማስቀመጥ የተቀበለ ሰው ቢኖር እጥፍ ያስከፍሉት። የሌባ ዋሻ የቀማኛ ጋሻ ሆኗልና።

√ አደራ ጠባቂ አደራውን እንደ ገንዘቡ አድርጎ መጠበቅ ይገባዋል። እንደ ገንዘቡ አድርጎ እየጠበቀ እያለ በእሳት አደጋ ወይም በተለያየ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ቢጠፋበት ተጠያቂ አይሆንም።

√ አደራ የተቀበለ ሰው አደራውን በእርሱ ቸልተኝነት ቢያጠፋው መክፈል ይገባዋል።

√ አደራን ጠብቆ መመለስ ለለመደ ነው እንጂ ላልለመደ ሰው መስጠት አይገባም።

√ የመጽሐፍ አደራን ላልተማረ ሰው መስጠት አይገባም። ባለማወቅ የጎታ መክደኛ ሊያደርገው ይችላልና።

:::::::::::

:::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሠላሳ

የሹመትን ነገር ይናገራል።

√ ሹመት የሚገባው ግብሩ ጠባዩ ያማረ ሰው ነው።

√ የተሾመ ሹመኛ ያለ ተንኮል ያለ ስንፍና የተሾመበት ገንዘቡ ቢጠፋበት መክፈል አይገባውም።

√ ጌታው ለሹሙ አንዲት በግ ግዛልኝ ብሎት ሹሙ ግን አንድ አንድ ብር የሚያወጡ ሁለት በጎች ቢገዛ ሁለቱም ለሾመው ለጌታው ይሁኑ።

√ ሹም ጌታው ሳይፈቅድ ሌላ ተወራጅ ሹም መሾም አይገባውም።

:::::::::::

:::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሠላሳ #አንድ

አገልጋይን ነጻ ማውጣት እንዲገባና አገልጋይን መግዛት እንዲገባ ይናገራል።

√ ሰው ሁሉ ከአዳም በመገኘቱ ነጻ ነው።ነገር ግን በጦር ወይም በሌላ ምክንያት አንዱ ሰው ለአንዱ በግድ ወይም በፈቃድ እንዲገዛ ያደርገዋል።

√ አገልጋይ ጸንሳ ሳለ ነጻ ብትወጣ በማኅጸኗም ያለው ሕጻን ነጻ ነው።

√ አገልጋይን ነጻ ማውጣት የትሩፋት ሥራ (መልካም ሥራ) ነው።

√ አገልጋይ በጌታው ፈቃድ ካህን ወይም መነኮስ ከሆነ ነጻ ይወጣል።

√ አማኝ አገልጋይ ከማያምኑ ሰዎች ካለ አማኙ ጌታ ገዝቶ ማምጣት ይገባዋል።

:::::::::::

:::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሠላሳ #ሁለት

የሹመትን ነገር ይናገራል።

√ አደራ ሰው ሊጠበቅለት ከጠባቂ ዘንድ አምኖ የሚያኖራት ገንዘብ ናት።

√ ምእመናን እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ዘመዶቻቸውን፣ የደከሙትን፣ የታመሙትን፣ ያረጁትን መርዳት ይገባቸዋል።

::::::::::::::::::::

ስለ መሸጥና መግዛት ይናገራል።

:::::::::::

√ ከሌባ መግዛት አይገባም

√ እሑድ፣ በጌታ በዓላት እና በእመቤታችን በዓላት መሸጥ መግዛት አይገባም።

√ በአደራ የተሰጠን ነገር መሸጥ አይገባም።

√ ሙቶ ያደረውን፣ የአውሬውን ትራፊ፣ መርዝነት ያላቸውን ፍጥረታት ሥጋን፣ እንዲሁም መርዝነት ያላቸው እፀዋትን መሸጥ አይገባም።

√ መሸጥ እና መግዛት በገዢ እና በሻጭ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባል።

:::::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሠላሳ #አራት

ስለ ተሳትፎ ይናገራል።

√ ተሳትፎ የሚለው አንዱ በከብት አንዱ በጉልበት ሆነው የሚነግዱት ንግድ ነው። በአንድነት ከገቡ በኋላ ልማቱም ጥፋቱም የጋራ ነው። አንዱ ሳይፈቅድ አንዱ በራሱ በተሳትፎው ላይ መወሰን አይገባውም።

:::::::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሠላሳ #አምስት

ስለ አገብሮና ተኃይሎ ይናገራል።

√ አገብሮ የሚለው የግድም የውድም ነው። ተኃይሎ ግን የግድ ነው።

√ ሃይማኖቴን አልክድም ብሎ መከራ የሚቀበል ሰው ቢገደል ሰማዕት ይባላል።

√ አንዱ አንዱን ሕግ አፍርስ፣ ግደል፣ ሰስን ብሎ ቢያገብረው አገብሮውን መቀበል አይገባም።

√ ተኃያሊ (ቀማኛ) ገንዘብ ቢዘርፍ ባዕለጸጋ ቢሆን ከወሰደው አምስት እጥፍ አድርጎ ለባለቤቱ ይመልስ፣ ይህን ካልቻለ እጥፍ አድርጎ ይመልስ፣ ይህንንም ካልቻለ ዓይነታውን ይመልስ፣ ይህንንም ካልቻለ ያለውን ያስከፍሉት።

√ ገንዘቡ ተገኝቶ ባለቤቱ ቢታጣ ይረባው ይጠቅመው ዘንድ ሊመጸውቱለት ይገባል።

::::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሠላሳ #ስድስት

ስለ መጠመን ስለማስጠመን {ስለ መከራየት፣ ስለማከራየት፣ ስለ ቅጥር?} ይናገራል።

√ ተጠማኝ {ተከራይ?) በቸልተኝነቱ ምክንያት የተጠመነውን ነገር ቢያበላሽ ይከፍላል።

√ እባብ ዘንዶ የሚበዛበትን ቦታ፣ የሚያሳምም ውሃ ያለበትን ጉድጓድና የመሳሰሉትን ማስጠመን አይገባም።

√ ማንኛውንም ገንዘብ የተጠመነ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ መዓት ታዞ ቢያጠፋበት ዕዳ የለበትም።

::::::::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሠላሳ #ሰባት

√ ሰው ሁሉ በቤቱ ጎረቤቱ የሚያዝንብትን ሥራ መስራት አይገባውም።

√ ሰውን ለመጉዳት ወይም ለማሳዘን ማናቸውንም ደንቃራ የሚያኖር ሰው ካለ ይቀጣ።

√ ከታች (Ground) የሚኖር ሰው ከላይ ያሉትን ሰዎች የሚረብሽ ጭስ ማጨስ አይገባውም። ከላይም የሚኖሩት ከታች ወዳሉት ሰዎች ቆሻሻ መጣል ወይም ውሃ ማፍሰስ አይገባቸውም።

√ ጎረቤት ቤት ሲሠራ ሌሎችን ቤቶች ከብርሃን እንዳይከለክል (እንዳይጋርድ) ሆኖ ይሰራ።

√ ማንኛውም ሰው የሰውን ሁሉ የጋራ ሜዳ ማፍረስ መቆፈር አይገባውም።

√ አጥር ማጠር የፈለገ ቢኖር ከጎረቤቱ ቤት አንድ ክንድ ርቆ ይጠር። ቤት መስራት ቢፈልግ ደግሞ ከጎረቤቱ ቤት ቢያንስ ስድስት ክንድ ርቆ ይሥራ። የውሃ ጉድጓድ ማውጣት ከፈለገ ደግሞ ቢያንስ ከቤቱ አምስት ክንድ ርቆ ያውጣ።

√ አንድ ሰው ራሱ በሚያዝበት በቦታው አውሬ ለማደን ወጥመድ ቢያጠምድ ጉድጓድ ቢቆፍር እና በወጥመዱ ከብት ወይም ሌላ ነገር ቢሞት ዕዳ የለበትም።

√ አጥሩ ወደ ህዝባዊ ጎዳናው አዘንብሎ ሳለ ሰዎች አስተካክለው ብለውት ቸል ብሎ ቆይቶ አጥሩ ተንዶ ሰው ቢገድል ባለቤቱ ተጠያቂ ይሆናል።

::::::::::

::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሠላሳ #ስምንት

ስለ ብድር ይናገራል። ከአንቀጽ 27 የሚለየው ይህኛው አበዳሪና ተበዳሪ በአንድ እየሰሩ ትርፉ የጋራ ነው። ይህ በዚህ ጉዳይ የሚናገር አንቀጽ ነው።

::::::::::

::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ሠላሳ #ዘጠኝ

ስለ ተአምኖ ይናገራል። ራሱን የቻለ አካለ መጠን ያደረሰ ሰው በእውነት በደሉን ቢናገር (ቢታመን) ተጸጽቶ ገንዘብ ሰርቄ ቀምቻለሁ ቢል ገንዘብ መክፈል ይገባዋል። ሕጻናት ግን ነፍስ ገድለናል ገንዘብ ወስደናል ቢሉ አይጸናም።

::::::::::

::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አርባ

√ ጠፍቶ የተገኘን ገንዘብ ለባለቤቱ መልስ።

√ ጠፍቶ የተገኘን ዕቃ፣ ንብረት ወይም ከብት የእኔ ነው ባይ ቢመጣ የእርሱ እንደሆነ ብዙ ምልክት ይናገር። የእርሱ መሆኑ ከተረጋገጠ ያገኘው ሰው በዳኛ ወይም በምስክር ፊት ይስጠው።

::::::::::

::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አርባ #አንድ

በገንዘቡ የሚያዝዝ አዛዥ ከመሞቱ በፊት ሦስት እጁን ለልጆቹ አንድ እጁን ለቤተክርስቲያን ሰዎች መስጠት ይችላል። አዛዥ ልጆች ባይኖሩት ግን ለፈቀደው ሰው የማውረስ ሥልጣን አለው። አንድ የጸነሰች እናት ለጽንሷ ውርስ ቢሰጠው እና ሁለት ልጆች ቢወለዱ ውርሱን እኩል ለሁለት ይካፈሉታል። አዛዥ ሲያወርስ ምስክር ሊኖር ይገባል።

::::::::::

Betemariyam Abebaw, [7/14/2022 9:58 AM]

[Forwarded from በትረማርያም አበባው]

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አርባ #ሁለት

ይህ አንቀጽ ስለ ርስት ይናገራል።

√ ከሟች ገንዘብ ለነዳያን መመጽወት መልካም ነው።

√ ኤጲስ ቆጶስ ኤጲስ ቆጶስነት ሳይሾም ያገኘውን ገንዘብ ሁሉ ለወደደው መስጠት ይገባዋል። ከተሾመ በኋላ ያገኘው ገንዘብ ግን ለቤተክርስቲያን ይሁን።

√ ሟች ዕዳ ቢኖርበት ወራሹ ይክፈል።

√ ባል ቢሞት ሚስት ከልጆቿ ጋር እኩል ትውረስ።

√ በመውረስ ጊዜ ሴትም ወንድም እኩል ይወርሳሉ።

√ መውረስ የሚገባቸው ከሕግ ሚስት የተወለዱ ናቸው።

√ ወራሽ የሌለው ሰው ገንዘቡ ለቤተ መንግሥት ይሁን።

+++++++

+++++++

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አርባ #ሦስት

ስለዳኞችና ስለ ምስክሮች ይናገራል።

√ የዳኛ የሚከተሉትን ነገሮች ሊያሟላ ይገባል።እነህም:-

- ጠባዩ ያማረ
- አይቶ ይፈርድ ዘንድ ዓይነስውር ያልሆነ
- የተማረ ቅን
- መስማት፣ መናገር የሚችል
- የማይቸኩል (ትዕግሥተኛ)
- እግዚአብሔርን የሚፈራ
- የማያዳላ
- ሕግ አዋቂ መጽሐፍ አዋቂ የሆነ

√ ዳኛ ጥሩ ፍርድ ከፈረደ በሰማይም በምድርም የከበረ ይሆናል።

√ ምስክሮችም የሚከተሉትን መሥፈርቶች የሚያሟሉ ሊሆኑ ይገባል።

  - እውነተኞች ይሁኑ
  - ደጋጎች ይሁኑ
  - ፪ እና ከዚያ በላይ ይሁኑ
  - ክፉ ያልሆኑ
  - ዘማዊ፣ ሌባ ያልሆኑ
  - ሰካራም፣ እብድ ያልሆኑ

√ ዳኛ ሰክሮ፣ ደክሞ፣ አንቀላፍቶ፣ አዝኖ፣ ተቆጥቶ፣ ደስ ብሎት ሳለ፣ ሰልችቶት ሳለ አይፍረድ።

√ ዳኛ አዝዞ ከሆነ መማል ይገባል። ያውም ግን በስመ እግዚአብሔር ወይም በወገኖቹ በቅዱሳን ነው እንጂ በጣዖትና በሌላ አይደለም።

√ ተጣልታችሁ ከሆነ ሳትታረቁ አትደሩ። የተጣሉትን ተስማምተው ይኖሩ ዘንድ አስታርቋቸው።

√ ክርስቲያን በአረማዊ ዳኛ መዳኘት አይገባውም።

√ ዳኛ ነውር ከተገኘበት ከሹመቱ ይሻራል።

√ ከሌላ ሰው ሰምቶ መመስከር አይገባም።

√ በሐሰት የመሰከሩ ይገረፉ

√ በሐሰት የሚመሰክሩ ብዙ ሰዎች ስላሉ ምስክሮቹንም ይመርምሯቸው።

:::::::::

Betemariyam Abebaw, [7/14/2022 9:58 AM]

[Forwarded from በትረማርያም አበባው]

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አርባ #አራት

ይህ አንቀጽ ስለ ነገሥታት ይናገራል።

√ ንጉሥ ነግሦ በዙፋኑ በተቀመጠ ጊዜ ፈጣሪውን እግዚአብሔርን መፍራት ይማር ዘንድ፣ ባለ ዘመኑ ሁሉ ይመለከተው ዘንድ፣ ልቡናው እንዳይታበይ መጽሐፍ ቅዱስ ይስጡት።

√ የንጉሡን ለንጉሥ ስጡ።

√ ንጉሥ የተሾመ አመጸኞችን ሊቀጣ ነው።

√ ነገሥታት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው።

√ ካህናት ግብር መክፈል፣ ዘመቻ መሄድ አይገባቸውም።

√ ጦርነት ስትገጥም ጠላቶችህ ብዙ ቢሆኑ እንኳ አትፍራ።

√ ምእመናን ወደ ጦርነት ሲሄዱ መቶ ጊዜ ኪርያላይሶን ይበሉ።

√ የምታነግሠው ንጉሥ ከምእመናን ወገን ይሁን።

√ ንጉሥ ዐላዊ ከሆነ ንጉሥ አይባልም።

√ ፈሪ ወደ ጦርነት አይሂድ። ይቅር።

√ ወደ ጠላት ሀገር ስትገባ ሽማግሌዎችን፣ ሕጻናትን፣ ሴቶችን፣ ባልቴቶችን፣ ካህናትን አታጥፋ

√ ከምርኮ ገንዘብ ስድስተኛው እጅ ለመንግሥት ይግባ። ቀሪውን የጦር አለቆች ወታደሮች በየደረጃቸው ይከፋፈሉት።

++++++

++++++

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አርባ #አምስት

+ ከቁጣ ተከልከል።

+ ፍትወታዊ እይታ አትይ።

+ በሐዲስ ኪዳን ምእመናን ከአሕዛብ ጋር ጎረቤት ሆነው መኖር ይችላሉ። {ነገር ግን ሃይማኖታቸውን እና ሥርዓታቸውን ጠብቀው መሆን አለበት}

+ መኳንንትን አትሳደብ

+ ግማሽ ጸጉራችሁን ብቻ ተላጭታችሁ ግማሹን ጉድሮ አድርጋችሁ አትተው።

+ ለሞተ ሰው ፊታችሁን አትንጩ።

+ በእድሜ ከአንተ የበለጠውን አክብረው።

+ መምህራን ካስተማሩህ ትምህርት አትውጣ

+ ባለን ዘመናችን በጎ ሥራ እንስራበት።

+ ከበጎ ነገር በቀር ከአንደበታችሁ ክፉ ነገር አይውጣ።

+ ትሕትናን በያዘ ልቡና በፍቅር ጸንታችሁ ኑሩ።

::::::::::::

::::::::::::

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አርባ #ስድስት

√ አምልኮ ስግደት (የባሕርይ) ለእግዚአብሔር ብቻ ይገባል።

√ ጣዖት የሚያመልኩ ሰዎች መንግሥተ ሰማያትን አይወርሱም።

√ ርኩስ መንፈስ እንዳይቀርባችሁ የጣዖታትን የሰይጣናትን ስም በምስጋና አትጥሩ።

+++++++

+++++++

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አርባ #ሰባት

√ መግደል ከዐበይት ኃጣውእ አንዱ ነው።

√ ከሰባት ዓመት በታች ያሉ ሕጻናት እና እብዶች ቢገድሉ አይፈረድባቸውም።

√ አንድን ሰው ዳኛ ግደል ብሎ አስገድዶት ቢገድል ሰውየው ነጻ ሲሆን ዳኛው ግን ይፈረድበታል።

√ ልጆች በአባታቸው፣ አባት በልጆቹ ደም አይሙቱ። የገደለው እና የተባበሩት ብቻ በፍርድ ይጠየቃሉ።

√ ባለ ደም ጠላቱን በእጁ ሊገድለው አይገባም። ኃጢአቱን መርምሮ ይፈርድበት ዘንድ ከዳኛ ያድርሰው እንጂ

√ ካህን ሰው ቢገድል ከሹመቱ ይሻር። ከዚያም መላ ዘመኑን ንሥሓ ይግባ {ቀኖና ይቀበል}

√ ሴት የገደለ ሰው 20 ዓመት ከምእመናን ይለይ።

√ አንድ ሰው አንዲትን ሴት በሥራዩ ጽንስ ቢያስወርዳት መላ ዘመኑን ንሥሓ ይግባ።

Betemariyam Abebaw, [7/14/2022 1:46 PM]

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አርባ #ስምንት

√ ኤጲስ ቆጶስ ዝሙት ሲሠራ ቢገኝ ከክህነቱ ይሻር።

√ ከማያምኑ ጋር ዝሙት የፈጸመ ሰው ቀኖና ተቀብሎ ቀኖናውን ሲጨርስ በካህኑ ቄደር ይረጭ።

√ ካህን ሚስቱ መሰሰኗን አውቆ ሊፈታት ባይወድ ከክህነቱ ይሻር።

።

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #አርባ #ዘጠኝ

√ ከንዋየ ቅድሳት የሰረቀ ቄስ ቢኖር ይለይ። የወሰደውንም አምስት እጥፍ አድርጎ ይመልስ።

።

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ኃምሳ

√ ሰካራሞች፣ ገዳዮች እና ዘማውያን መንግሥተ ሰማያትን አይወርሷትም።

√ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስካርን "የፈቃድ እብደት" ይላዋል።

√ እናት አባቱን የሚበድል ልጅ የእናት የአባቱን ርስት አይውረስ።

√ ወንድም የወንድሙን ኃጢኣት መግለጥ አይገባውም።

።

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ኃምሳ #አንድ

√ ወንዶች ጸጉራቸውን አያሳድጉ። ሲቆረጡ ጋሜ ቁንጮ አድርገው አያስተርፉ።

√ ወንዶች ጺማቸውን አይላጩ

√ በሐዲስ ኪዳን መገዘር ልማድ እንጂ ከመጽሐፍ የተገኘ አይደለም።

√ ኃጢአትን መታመን መንፈሳዊ ፈውስ ነው።

√ በሥርዐት ጉዳይ እንደየዘመኑ ሊቀ ጳጳሳት የተጻፈውን ማሻሻል፣ በተጻፈው መጨመር ይችላል። መሠረተ እምነትና የመጻሕፍት ንባባቸውና ትርጓሜያቸው ግን አይለወጥም።

።

#ፍትሐ #ነገሥት #አንቀጽ #ኃምሳ #ሁለት

√ ለመዋቲ ልጅ፣ ዘመድ ባይኖረው ገንዘቡ ለቤተክርስቲያን ይሁን።

√ አባቱ ቢሞት ልጁ ቢኖር አባቱ ይወርሰው የነበረውን ይውረስ።

።

።

አነሳስቶ ላስጀመረን

አስጀምሮም ላስፈጸመን

ልዑል እግዚአብሔር

ምስጋና ይገባል።